# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 002 መስከረም 2 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የራስን ምርት የመጠቀም ባህል የሚያስገኛቸው በረከቶች

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**
**ዜና ትንታኔ**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በበርካታ ከገጸ ምድርና ከከርሰ ምድር በሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች የበለፀገች መሆኗ ይታወቃል፡፡ ለየትኛውም አገልግሎት ጥቅም ላይ ለሚውሉ ምርቶች የሚሆን የጥሬ እቃ ግብዓቶችንም ታድላለች፡፡ የተፈጥሮ ሀብት ባለፀጋነቷ እሙን ቢሆንም፣ ያላትን ሀብት በአግባቡ መጠቀም ባለመቻሏ አስፈላጊ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ከማምረት ይልቅ በብዛት ከውጭ እያስገባች ነው፡፡

መንግሥት የሀገር ውስጥ አምራቾችን ለማበረታታት የተለያዩ ርምጃዎችን መውሰዱ በመጠኑም ቢሆን፣ በአምራቹ ዘንድ መነቃቃትን የፈጠረ ቢሆንም ምርቶች በስፋት ወደ ገበያ መውጣት አልቻሉም፡፡ የሀገር ውስጥ ምርቶችን ማበረታታትና የገበያ ትስስርን የመፍጠር ዓላማን ይዘው በሚሰናዱ አውድ ርዕዮች ላይም “እውነት በሀገር ልጅ የተመረቱ ናቸውን?” የሚያስብሉ ጥራት ያላቸው ምርቶች ለእይታ ቢቀርቡም በሚፈለገው ልክ ገበያን መያዝ አለመቻላቸውም በተደጋጋሚ ይደመጣል፡፡

**የራስን ምርት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**






# ለውጣ ውረድ ያልተበገረው የህዳሴ ግድብ

**ሞገስ ጸጋዬ**

የታላቁ የህዳሴ ግድብ በርካታ ፈተናዎችን ተሻግሮ አሁን ያለበት ደረጃ ደርሷል። ግድቡ አሁን ላይ ወደ ኋላ ከ205 እስከ 10 ኪሎ ሜትር ተኝቷል። ጥልቀቱ 133 ሜትር ደርሷል። ይህም የጣናን ኃይቅ እጥፍ ሆኗል። 62 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢክ ውሃ ይዟል። አራት ተርባይኖች ኃይል እያመነጩ ሲሆን በቀጣይ አራት ወራት ውስጥም ወደ ሰባት ከፍ ይላል።


የግድቡ ግንባታም በቀጣይ አንድ ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል። የህዳሴ ግድብ አሁን የደረሰበት ደረጃ ለመድረስ ከምሥረታው ጀምሮ በርካታ ጫናዎችንና ውጣ ውረዶችን አልፏል። ይሁን እንጂ ፈተዎችንና ውጣ ውረዶችን አልፎ ለስኬት በቅቷል፤ ፍሬውንም መቅመስ ጀምረናል።



ከሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የታላቁን ህዳሴ ግድብ አስመልክቶ እንደገለጹት፤ ባለፉት አምስት ዓመታት ኢትዮጵያ በተለያየ ግንባር በተለያዩ ችግሮች ተይዛ ሳለች 15 ሺህ የሚጠጉ የውጭ ኃይሎች በህዳሴ ግድብ ጉዳይ ብቻ አሰማርተውብናል። ሲሚንቶ አምርቶ አጓጉዞ እስከ ህዳሴ ለማድረስ 15 ሺህ የሚጠጋ የተለያየ ስም ያላቸው ለውጭ የተገዙ ሰዎች ህዳሴን ለማስተጓጎል ሞክረዋል። ብዙ ጊዜና ሕይወት አጥፍተዋል።

የኢትዮጵያውያን ሊገነዘቡ የሚገባቸው ለህዳሴን ሃሳብ፣ ገንዘብና ጊዜ ብቻ አልገነባውም፤ የገነባው ደም ጭምር ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ብዙ ዋጋ ከፍለንበታል፤ ህዳሴ ብዙ ሀብት

**ለውጣ ውረድ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**



# “የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት” መስከረም አጋማሽ ላይ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የቱሪዝም መረጃ የሚያዝበት “የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት” በመስከረም አጋማሽ 2017 ዓ.ም ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፉ በሰጠው ትኩረት ከአምስቱ የሀገር በቀል የሪፎርም አጀንዳዎች ውስጥ በማካተት ዘርፉን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል። የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ከማስተዋወቅና ከማልማት በተጨማሪ የቱሪዝም መረጃ የሚያዝበት ሥርዓት መበልጸጉን አስታውቀዋል።

የበለጸገው ሥርዓት “የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት” ሲሆን፤ በመስከረም አጋማሽ 2017 ዓ.ም ለሕዝብ ይፋ እንደሚሆን አመላክተዋል።

የቱሪዝም አገልግሎት ጥራትን ለማሳደግም

**“የቱሪዝም ሳተላይት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**




# በአዲሱ ዓመት የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት እንሠራለን ሲሉ ወጣቶች ገለጹ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲሱ ዓመት ያሉብንን ችግሮች በጋራ በመፍታት በአዲስ መንፈስ በመተጋገዝና በመተባበር የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት እንሠራለን ሲሉ ወጣቶች ገለጹ።

ወጣት ሄኖክ ፍቃዱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገረው፤ በአዲሱ ዓመት የበጎ አድራጎት ሥራዎችን በስፋት ለማከናወን አቅዷል። በዚህም የተቸገሩ እናቶችን፣ አቅመ ደካሞችን እና ሌሎች ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን በሚችለው አቅም ሁሉ ለማገዝ ራሱን እያዘጋጀ ነው።

ወጣቶች በአዲሱ ዓመት ጸብ ከሚያስነሱ ድርጊቶች ራሳቸውን ሊጠብቁ ይገባል። ይህም ለሀገር ሰላምና እድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን የገለጸው ወጣት ሄኖክ፤ ሁሉም ወጣት በአዲሱ ዓመት ችግሮችን በንግግር ለመፍታት ጥረት ማድረግ አለበት ብሏል።

ይህም የተሻለች ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚደረገው ጥረት አንዱ ጅማሮ ሊሆን እንደሚችል በማንሳት፤ መንግሥት ያለበት ችግር በመለየት ለመፍታት መጣር እንዳለበት እና ወጣቱ ደግሞ ራሱን ለማሻሻል ቀን ከለሌት መትጋት እንዳለበት ገልጿል።

ከምንም በላይ ለኢትዮጵያ እድገት መሠረት የሚሆነው የመረዳዳት፣ የመደጋገፍና የመተባበር እሴት መሆኑን የገለጸው ወጣት ሄኖክ፤ ወጣቱ በአዲሱ ዓመት በበጎ አድራጎት ማህበራት በኩል የተቸገሩ ወገኖችን መርዳት አለበት። ይህም ለሀገር በረከት የሚያስገኝ መሆኑን ተናግሯል።


ወጣት ሄኖክ ፍቃዱ


ወጣት ጫላ አሰፋ

አዲስ ዓመት የተሻለች ኢትዮጵያን ማለትም ሰላሟ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን እናያለን የሚል እምነት እንዳለው ገልጾ፤ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፏል።

ወጣት ጫላ አሰፋ (ኢ/ር) በበኩሉ፤ ወጣቱ ባሳለፍነው ዓመት ያልሠራቸውንና መሥራት ያለበትን ሥራዎች በአዲሱ ዓመት ለማሳካት መጣር አለበት። ወጣት የአዲስ ሃሳብ ባለቤት እንደሆነ እና ይህንን በአግባቡ ከተጠቀመው ለኢትዮጵያ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት ገልጿል።

በአዲሱ ዓመት የጥላቻን ግምብ በማፍረስ የሰላም፣ የጤና እና የእድገት መሠረት ለመጣል መዘጋጀቱን የገለጸው ወጣት ጫላ፤ ከዚህ አንፃር ወጣቱ አዲሱን ዓመት አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት ኢትዮጵያን ከፍ ሊያደርግ ይገባል ብሏል።

ወጣቶች በሰላም ግንባታ፣ በአካባቢ ጥበቃ እና ሕዝቦችን ለማቀራረብ በሚከናወኑ ሥራዎች ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ወጣት ጫላ በአዲሱ ዓመት በዚህ ተግባር ግንባር ቀደም ተሰላፊ እንደሚሆን ተናግሯል።

አዲሱን ዓመት በአዲስ መንፈስና ጉልበት የተሻለች ኢትዮጵያን በጋራ ለመገንባት መረባረብ እንደሚገባም ጠቁሟል።



# 750 ቤተሰቦችን “በሶላር ሆም ሲስተም” ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከዋናው ኤሌክትሪክ መስመር ርቀው የሚገኙ 750 ሺህ አባወራዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክና የብርሃን ተደራሽነት ፕሮግራም (ADELE) በዓለም ባንክ በሚደገፍ የ50 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዶላር በጀት በቀጣይ አምስት ዓመታት ሊተገበር መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በሚኒስቴሩ የኢነርጂ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ኢ/ር ሱልጣን ወሊ እንደገለጹት፤ ፕሮግራሙ በአምስት ዓመታት ውስጥ ገጠራማ የሆኑና ከዋናው የኤሌክትሪክ መስመር ከ2 ነጥብ 5 እስከ 50 ኪሎ ሜትር ርቀው የሚገኙ አባወራዎችን የሶላር ሆም ሲስተም ተጠቃሚ ለማድረግ ታላሚ ተደርጎ የሚተገበር ነው ብለዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ በቀጣይ ሁለት ዓመታት በፕሮግራሙ በሀገሪቱ 400 ወረዳዎች 350 ሺ አባወራዎችን የሶላር ሆም ሲስተም ተጠቃሚ ለማድረግ 10 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ተበጅቶ ወደ ተግባር መገባቱንም ገልጸዋል፡፡

ዶ/ር ኢ/ር ሱልጣን ወሊ የመጀመሪያ ዙር የፕሮግራሙ አካል የሆነውን በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ከ 45 ሺ በላይ አባወራዎችን በሰባት ክልሎች የሶላር ሆም ሲስተም ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችለውንና 150 ሚሊዮን ብር ወጪ የሚደረግበትን የውል ስምምነት ከዘጠኝ የሶላር ቴክኖሎጂ አቅራቢና አከፋፋይ ሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር ተፈራርመዋል፡፡

በሶላር ሆም ሲስተም ቢያንስ ለአንድ ቤተሰብ አባላት ከአምስት እስከ አስራ ሁለት ዋት ፒክ ሃይል በማመንጨት ለመብራት፣ ለቻርጅ፣ ለሬዲዮና ለሌሎች መሰል አገልሎቶች ጥቅም ይሰጣልም ብለዋል፡፡

በፊርማ ሥነሥርዓቱ የተገኙት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶ/ር ኢ/ር ሀብታሙ ኢተፋ፤ ድርጅቶቹ በገቡት የውል ስምምነት መሠረት ጥራት ያለው ሥራ በመሥራት ሃላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው በማሳሰብ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱም አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚደርግላቸው አስታውቀዋል፡፡

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ውል የወሰዱ ሀገር በቀል ድርጅቶች ችግሩን በይበልጥ ተረድተው መንግሥት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በሃይሉ ዘርፍ ተጠቃሚ ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት ዐሻራቸውን ሲያኖሩ ወገኖቻቸውን እየጠቀሙ መሆኑን በመረዳት ለቀጣዩ ሥራቸው ውጤታማነት ስንቅ የሚሆናቸውን መልካም ሥራ በመሥራት ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ሚኒስትሩ አሳስበዋል፡፡

# የአፈር ማዳበሪያን በመስከረም ወር በቅናሽ ገዝቶ ለማስገባት ዝግጅት ተደርጓል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የአፈር ማዳበሪያን በ2017 ዓ.ም መስከረም ወር ከዓለም ገበያ በቅናሽ ገዝቶ ወደሀገር ውስጥ ለማጓጓዝ ዝግጅት መደረጉን የግብርና ሚኒስቴር ገለጸ።

የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ለ2017/18 ዓ.ም ምርት ዘመን እያደገ የመጣውን የግብርና ግብዓት የመጠቀም ፍላጎት ለማሟላትና ምርትን ለማሳደግ 25 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ለመግዛት ዝግጅት እየተደረገ ነው።

በ2017/18 ዓ.ም የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያን መስከረም ወር በቅናሽ ዋጋ በመግዛት ወደ ሀገር ውስጥ ለማጓጓዝ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር አስፈላጊው ዝግጅት መደረጉን ተናግረዋል።

በቀጣይ የአርሶ አደሩን የግብዓት ፍላጎት የሚመጥን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት እንዲኖር ቀደም ብሎ የዝግጅት ሥራዎች መከናወናቸውን አንስተዋል።

በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን ተሻሽሎ ተግባራዊ የተደረገው የግብርና ግብዓት የግዥ ሥርዓት በፊት የነበረውን የአፈር ማዳበሪያ እጥረት ችግር መፍታቱን አስታውሰው፤ 20 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ግዥ በመፈጸም ከ18 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሚሆነው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባና ከዚህ ውስጥም 87 በመቶው ለአርሶ አደሩ ማሰራጨት ተችሏል ብለዋል።

በ2017/18 የምርት ዘመንም 25 ሚሊዮን ኩንታል በመግዛት በወቅቱ ወደ ሀገር ገብቶ ለአርሶ አደሩ እንዲሠራጭ አቅጣጫ መቀመጡን ገልጸው፤ በ2014/15 ዓ.ም በምርት ዘመን የነበረውን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ችግር የግዥ ሥርዓቱን በማሻሻል፣ አዲስ ቦርድ በማቋቋም፣ የቴክኒካል ኮሚቴ በማዋቀርና የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት ችግሩን የመፍታት ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ እያጋጠሙ ባሉ የፀጥታ ችግሮች ምክንያት በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን በግብዓት አቅርቦት በኩል የተስተዋሉ ውስንነቶች እንደነበሩ አስታውሰው፤ ውስንነቶቹን ሙሉ ለሙሉ በመቅረፍ በቀጣይ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ከወዲሁ በትብብር መሥራት እንደሚገባ አመላክተዋል።

ግብርናውን ለማዘመን፣ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትን ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ማክሮ ኢኮኖሚን ውጤታማ ለማድረግ የአፈር ማዳበሪያ በጥራትና በፍጥነት ለአርሶ አደሩ መቅረብ እንዳለበት አብራርተዋል።

የ2017/18 ዓ.ም የምርት ዘመን ግብርና ግብዓት አቅርቦትን፤ ተደራሽነትን በማስፋት ምርታማነትን ለማሳደግ በየወረዳው ያሉ የግብርና ባለሙያዎች፣ የህብረት ሥራ ማህበራት፣ የክልል ቢሮዎችና የፌዴራል ተቋሟት የሚያከናውኑትን የቅንጅት ሥራ ማጠናከር እንዳለባቸው ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ትራንስፖርትና ሎጀስቲክ ሚኒስትር አለሙ ስሜ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በ2016/17 ዓ.ም የምርት ዘመን የአፈር ማዳበሪያ እጥረት እንዳይገጥም ያላሰለሰ ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

የማዳበሪያ ከተገዛ በኋላ ወደሀገር ውስጥ በፍጥነት እንዲገባ የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ሚኒስትሩ አሳውቀዋል።

# የነገዋ ኢትዮጵያ ተስፋ ታዳጊዎች

**ዜና ሀተታ**
**ዳግማዊት አበበ**

የነገዋ ኢትዮጵያ በኢኮኖሚ ያደገች ፣ በቴክኖሎጂ የላቀች ፣ ሰላሟ የተረጋገጠ እንድትሆን የተለያዩ ተግባራት እየተከናወነ ነው። ከእነዚህ ተግባራት አንዱ ታዳጊዎች በቴክኖሎጂው ዘርፍ ያላቸውን እምቅ አቅም ወደ ተግባር እንዲለውጡ ምቹ ዕድል መፍጠር ነው።

ከእነዚህ ምቹ ሁኔታዎች አንዱ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት 200 የኤ አይ ሰመር ካምፕ መርሃ ግብር በቴክኖሎጂው ተሠጥኦ ያላቸውን ታዳጊዎች እያሠለጠ ይገኛል።

ታዳጊ መልካም አስራት ፤ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን በመጠቀም የኮሌራ በሽታ ከመከሰቱ በፊት ውሃ ውስጥ የኮሌራ ቫይረስ መኖርና አለመኖሩን የሚያሳውቅ መሣሪያ መሥራቷን ትናገራለች።

የ10ኛ ክፍል ተማሪና ከዲላ ከተማ እንደመጣች የምትናገረው መልካም ሥልጠና እድሉን ያገኘሁት ክረምትን ቤት ከማሳልፍ በሚል ኢንስቲትዩቱ ባወጣው ማስታወቂያ መሠረት በኦንላይን ተመዝግቤ ነው ትላለች። ከዚህ በፊት በዲላ ከተማ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን እንደሠራችም ትገልጻለች።

በአገኘችው የኤ አይ የክረምት ሥልጠና የኮሌራ መመርመሪያ መሣሪያውን እንድሠራ ያነሳሳት በምትኖርበት የዲላ ከተማ ሁሌም ክረምት ሲሆን በሽታው መቀስቀሱና ለህብረተሰቡ ስጋት መሆኑ ነው የምትለው ታዳጊዋ፤ በሰራሁት መሣሪያም ከዚህ በኋላ የበሽታው ስም እንዳይነሳ እንደማደርግ ተስፋ አለኝ ብላለች።

መሣሪያው በሽታው ከመከሰቱ በፊት ውሃ ውስጥ ያለውን የሚመረምር ሲሆን ከተከሰተም በኋላም የበሽታው መጠን ምን ያህል እንደሆነ በመመርመር ፈጣን ምላሽ የሚሰጥ ነው ስትል ገልጻ፤ ታማኒነቱም 95 በመቶ ነው፤ ይህም አንድ የቤተ ሙከራ (ላብራቶሪ) ባለሙያ




ከሚሰጠው ምላሽ እኩል ነው ስትል ታብራራለች።

ታዳጊዋ፤ ወደፊት መሣሪያው ላይ ተጨማሪ ፈጠራዎችን በማከልና ሥራ ላይ በማዋል ከኢትዮጵያ አልፎ የአፍሪካን የኮሌራ በሽታ ችግር የመቅረፍ እሠራለሁ ትላለች።

የክረምት ቆይታዬ የተለያዩ እውቀቶችን እንዳገኝ እንዲሁም ይህን ማሽን በኤ አይ አማካኝነት እንደሠራ እድሉን አግኝቻለው የምትለው ታዳጊ መልካም፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሠልጣኞች በሚፈልጉት ዘርፍ በተግባር መሠልጠናቸው የሚያስደስትና ውጤታማ ቆይታ እንዲኖር አድርጓል ብላለች።

የግብርናው ዘርፍ ላይ የሚሠራ ሮቦት የሠራው ደግሞ ታዳጊ አብዱራህማን ሙህዲን ነው። ታዳጊው የፈጠራ ሥራውን የሠሩት በቡድን መሆኑን ተናግሮ፤ ሮቦቱ አንድ ሰብል ተዘርቶ ጎተራ እስከሚገባ ድረስ የተለያዩ እቃዎች እየተቀየሩለት የሚሠራ ነው ይላል።

በኢትዮጵያ 80 በመቶ በላይ የሚሆነው ዜጋ በግብርናው ዘርፍ ላይ ያለ ነው። እንዲህም ሆኖ ሀገራችን በምግብ እራሷን አልቻለችም። ይህም የሆነበት ምክንያት አብዛኛው የግብርናው ዘርፍ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአስተራረስ ዘዴ ባለመከተላችን ነው ሲል ይገልጻል።

የፈጠራ ሥራውን ልንሠራ የቻልነው ብቸኛው ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን እድትችል ማድረግ የሚቻለው የግብርና ዘርፉን በሮቦቶች በመደገፍ መሆኑን በመረዳት ነው።

የሠራነው የፈጠራ ሥራ አሁን ኢትዮጵያ ላይ ተግባራዊ የሚደረገውን የእርሻ ስልት ማለትም የተለያዩ ማሽነሪዎች በመጠቀም ማረስ፣ ማለሰለስ፣ መዝራት፣ ፀረ ተባይና አረም መርጨት እንዲሁም ማጨድ በአጠቃላይ ከ10 በላይ ማሽነሪዎች የሚሠሩትን ሥራ ከስር ያለውን ጥርስ ብቻ በመቀየር በአንድ ሮቦት እንዲከወን የሚያደርግ ነው ሲል ያብራራል።

ይህም ለተለያዩ ማሽነሪዎች የሚወጡ ወጪዎችንና ጊዜን የሚቆጥብ ነው ። በተጨማሪም ሮቦቱ አየር ሁኔታንና አፈር አሲዳማነትን የሚቆጣጠር ቴክኖሎጂ የተገጠመለት በመሆኑ ጥሩ ምርት ለማምረት የሚያስችል ነው ሲል ይገልጻል።

የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ዋና ዳይሬክተር ወርቁ ጋቸና (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የመጡ ሶስት ሺህ 500 ተማሪዎች ተመዝግበው መስፈርቱን ያሟሉ 200 ተማሪዎች በዘንድሮው ክረምት እንዲሰለጥኑ መደረጉን ገልጸዋል።

ሥልጠናው በአምስት ዘርፎች እንደተከናወነ ያነሱት ዋና ዳይሬክተሩ በዘርፉ ብቁና ተወዳዳሪ የእውቀት ባለቤት የሆኑ ወጣቶችን ማፍራት ተችሏል ብለዋል።

ሥልጠናው በዘርፉ እውቀት ባላቸው አሠልጣኞች ከተሟላ ግብዓት ጋር የቀረበ ሲሆን የክረምት ሥልጠናው የኢትዮጵያ ወጣቶች በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ችግር ፈቺና በዓለም ተወዳዳሪ የሆኑ ፕሮጀክቶችን እንዲሠሩ ያደረገ ነው ያሉት።

ከሰሞኑ የኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ለሁለት ወራት በአምስት ዘርፎች ሲያሠለጥናቸው ቆየውን 200 የኤ አይ ሰመር ካምፕ ሠልጣኞች ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት አስመርቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ተመራቂዎቹ በሰመር ካምፕ መርሐ ግብር የተሰጣቸው ሥልጠና በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው "የ5 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ኮደርስ ኢኒሼቲቭ" ሥልጠና ቁልፍ መሠረት መሆኑን ገልጸው አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ መልካም ፍሬ የሚሰጥ ምርጥ ዘር መሆኑን ነው የገለጹት።

# ከተማ አስተዳደሩ የመማር ማስተማር ሥራውን በታቀደው ጊዜ ለመጀመር ዝግጅት አድርጓል

- **ከ140 ሺህ በላይ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል**

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የ2017 የትምህርት ዘመን የመማር ማስተማር ሥራ በታቀደው ጊዜ ለመጀመር ዝግጅት ማድረጉን የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከ140ሺህ በላይ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ተጠቁሟል

የቢሮው ምክትል ኃላፊ አቶ አቡበከር አብዱሽ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ አራት የገጠርና ዘጠኝ የከተማ ወረዳዎች ከፍተኛ ንቅናቄ በማካሄድ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህጻናት ወደ ትምህርት ቤት እንዲመጡና የ2017 የትምህርት ዘመን የመማር ማስተማር ሥራ በታቀደው ጊዜ ለመጀመር በርካታ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

በዚህም በከተማ በአስተዳደሩ በሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ከነሐሴ 27 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የተማሪዎች ምዝገባ መካሄድ የተጀመረ መሆኑን ገልጸው፤ የመማር ማስተማር ሥራው መስከረም 07 ቀን 2017ዓ.ም በተቀመጠው ሀገራዊ አቅጣጫ መሠረት እንደሚጀመር አቶ አቡበከር ጠቁመዋል።

ባለፈው ዓመት 122ሺህ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር መቻሉን ያስታወሱት አቶ አቡበከር፤ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናትን ጨምሮ በአዲሱ የትምህርት ዘመን ከ140ሺህ በላይ ተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል።

እንደ ምክትል ኃላፊው ገለጻ፤ አነስተኛ የኢኮኖሚ መሠረት ያላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ተለይተው የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ተግባርም የተማሪ ቁጥርና ውጤታማነት እጅጉን እንዲጨምር አድርጓል፡፡

የምገባ ፕሮግራሙ ከአካባቢው ባለሀብቶች ጋር በመተባበር እየተከናወነ መሆኑን አውስተው፤ በአዲሱ የትምህርት ዘመንም የከተማ አስተዳደሩ ለምገባ ይመድብ የነበረውን በጀት በማሳደጉ በተለይም በገጠር ትምህርት ቤቶች ፕሮግራሙን አጠናክሮ ለማስቀጠል አቅጣጫ ተቀምጧል ብለዋል፡፡

የመግዛት አቅም የሌላቸውን ተማሪዎች ለመደገፍ የህብት አሰባሳቢ ኮሚቴ በማዋቀር የደብተር፣ የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም)ና ሌሎች ድጋፎችን ለማድረግ ሀብት የማሰባሰብ ተግባር በመከናወን ላይ መሆኑን አመልክተው፤ ትምህርት ቤቶች እንደተከፈቱ ለተማሪዎች የማዳረስ ሥራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በከተማ አስተዳደሩ ከሚገኙ 87 የአንደኛ ደረጃና 13 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ቤቶች ውስጥ አብዛኞቹ እድሳት የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ የትምህርት ቤቶቹን ጥራት ለማሻሻል ይሠራል፡፡

‹‹ትምህርት ለትውልድ›› በሚል መሪ ቃል እንደ ሀገር የተጀመረውን የትምህርት ቤቶችን ደረጃ የማሻሻል ንቅናቄ ተከትሎ መማሪያ ክፍሎችን የማደስ፣ የተማሪዎች መቀመጫና ጥቁር ሰሌዳ የማሟላት ተግባር ሲከናወን ቆይቷል፡፡ ንቅናቄውም ውጤታማ እንደሆነ መገንዘብ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ መደረጉን ተከትሎ ከተማ አስተዳደሩ ከቅድመ 1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል በርካታ ቁጥር ያለው የመማሪያ መጽሐፍት ህትመት በማከናወን ለተማሪዎች ተደራሽ ማድረግ መቻሉን አውስተዋል፡፡

ተጨማሪ የመማሪያ መጽሐፍት በህትመት ላይ የሚገኝ በመሆኑ በ2017 ዓ.ም ለእያንዳንዱ ተማሪ ለግሉ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንዲሁም ለሁለተኛ ደረጃ የሚያስፈልገው መጽሐፍ በትምህርት ሚኒስቴር በኩል እየቀረበ ሲሆን በመጀሪያው ዙር አንድ መጽሐፍ ለሶስት ማዳረስ እንደተቻለና ሁለተኛው ዙር በቅርቡ እንደሚደርስ አመላክተዋል፡፡

የድሬዳዋና አካባቢዋ ነዋሪ እድሜው ለትምህርት የደረሰ ህጻን ወደ ትምህርት ገበታ እንዲገባ በመተባበር የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት በሚደረገው ጥረት ሁሉም ዜጋ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

# በባለሥልጣኑ የተጀመረው ወረቀት አልባ የሶፍትዌር ልማት ፕሮጀክት 58 በመቶ ተከናውኗል

**ስሜነህ ደስታ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን በ150 ሚሊዮን ብር የሚያከናውነው ወረቀት አልባ የሶፍትዌር ልማት ፕሮጀክት 58 በመቶ መድረሱን አስታወቀ፡፡

ባለሥልጣኑ በዓመቱ ውስጥ የተሠሩ ሥራዎችን ነሐሴ 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ከባለድርሻ አካላት ጋር በኔክሰስ ሆቴል በገመገመበት ወቅት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ሙሉ እመቤት ታደሰ እንደገለጹት፤ የባለሥልጣኑን ማንኛውም ሥራ ወረቀት አልባ ለማድረግ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ ጋር በመተባበር 150 ሚሊዮን ብር የሚያወጣ የሶፍትዌር ፕሮጀክት እየተከናወነ ነው፡፡

ፕሮጀክቱ 58 በመቶ መከናወኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ሶፍትዌሩ አስራ ሁለት ተግባራትን ዲጂታላይዝ የሚያደርግ መሆኑንና በ2017 ዓ.ም. ተጠናቆ ወደ ሥራ ለማስገባት ከፍተኛ ርብርብ እንደሚደረግ ተናግረዋል፡፡

እንደዋና ዳይሬክተሯ ማብራሪያ ይህ ፕሮጀክት ለዚህ ደረጃ መብቃቱ ከቢሮውና ከባለሥልጣኑ በላይ የከተማው አስተዳደር የሚያደርገው ክትትልና እገዛ ከፍተኛ ነው፡፡

በባለሥልጣኑ በኩል የተሰጡ የብቃት ማረጋገጥ ሰርተፍኬት፣ የጤና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጥ ብቻ ሲታይ በዓመቱ ውስጥ በጥቂት ሠራተኞች ከ 14 ሺህ በላይ ሰርተፍኬት የተሰጠ መሆኑን ያነሱት ወይዘሮ ሙሉእመቤት፤ ይህ ከእቅድ በላይ የተሠራ ተግባር በሠራተኞቹ ከፍተኛ የሥራ ትጋት የተገኘ ውጤት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም ፋይሎቹ የድሮ ፋይሎች በመሆናቸው አቧራ ማራገፍ፣ ፈልጎ ማግኘት እና በቁርጠኝነት ሳይሰለቹ ዕለት በዕለት ተግቶ መሥራትን የሚጠይቅ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ ጋር በመተባበር እየለማ ያለው ወረቀት አልባ የሶፍትዌር ፕሮጀክት ተግባራዊ ሲሆን አሠራሩ እጅግ ስለሚዘምን ይህን መሰል ችግሮች ይወገዳሉ ብለዋል፡፡

በዕለቱ በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ የቁልፍ ተግባራት



ወይዘሮ ሙሉ እመቤት ታደሰ

ግቦች አፈጻጸም ሪፖርት ሲቀርብ እንደተጠቀሰው ክትትል እና ቁጥጥር ከተደረገባቸው የጤና ተቋማት ውስጥ 109 ተቋማት ጉድለት የተገኘባቸው ሲሆን 87 ተቋማት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 21 ጊዜያዊ እሽጋ እና 1 ተቋም ፍቃድ የመሰረዝ ርምጃ ተወስዶባቸዋል፡፡

ከመድኃኒት ተቋማት ውስጥ ደግሞ 116 ተቋማት ላይ ችግር የተገኘባቸው ሲሆን 77 ተቋማት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 38 ተቋማት ላይ ጊዜያዊ እሽጋ እና 1 ተቋም ፍቃድ የመሰረዝ ርምጃ የተወሰደ ሲሆን 90 ሺህ 584 ኪ.ግ. የሚመዝንና አርባ ሰባት ሚሊዮን አምስት መቶ አርባ ሰባት ሺ አራት መቶ ዘጠና ስድስት ብር ከ84 ሳ.ም. ዋጋ ያላቸው መድኃኒቶች ተወግደዋል፡፡

የምግብ እና ጤና ነክ ተቋማት ውስጥ 941 ተቋማት ላይ ችግር የተገኘባቸው ሲሆን 855 ተቋማት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ 83 ተቋማት ላይ ጊዜያዊ እሽጋ እና 3 ተቋም ፍቃድ የመሰረዝ ርምጃ ተወስዷል፡፡

በአጠቃላይ በዓመቱ የተወገዱ ጊዜ ያለፈባቸውና የተበላሹ ምግቦች 132 ሺ 250 ኪ.ግ. በቁጥጥርና የኦፕሬሽን ሥራ በመሥራት 13 ሚሊዮን 345 ሺ 270 ብር ዋጋ ያለው ጊዜ ያለፈባቸውን ምርቶች እንዲወገዱ ተደርጓል ሲሉ ዳይሬክተሯ ጠቅሰዋል፡፡

ከዚህ ውስጥ ስድስት ሚሊዮን ብር የሚገመት 109 ማዳበሪያ ቅቤ የናሙና ምርመራ በማድረግ በውጤቱም መሠረት ከባዕድ ጋር የተቀላቀለና ለጤና አስጊ መሆኑ በመረጋገጡ እንዲወገድ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ልማታችን የህልውናችን ጉዳይ ነው!

ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ሉዓላዊነታቸውን አስጠብቀውና አስከብረው ዘመናትን ካስቆጠሩ ጥቂት የዓለም ሀገራት አንዷ ነች። ሉዓላዊነታችንን በማስከበር ሂደትም ከፍተኛ መስዋእትነት የጠየቁ አውደ ትግሎችን በየዘመኑ አካሂደናል። በየአውደ ወጊያው ባለድል የሆንበት አይበገሬ የጀግንነት መንፈስም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ አሁን ላይ የነጻነት ተምሳሌት አድርጓታል።

ይህ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኘው ከአትንኩኝ ባይነት የሚመነጨው የነጻነት ገድል ትርክቷ፤ በየዘመኑ ለሚመጡ ትውልዶች የማንነት እና የብሄራዊ ክብር፤ ከመሆን ባለፈ ስለ ነጻነት ለተደረጉና እየተደረጉ ላሉ ሕዝባዊ ትግሎች መንፈሳዊ መነቃቃት እና የአሸናፊነት ሥነልቦና በመሆን እያገለገለ ነው።

ይህም ሆኖ ግን እንደሀገር የመጣንበት ፤ የድህነት እና የኋላ ቀርነት ጉዞ በብዙ ተጋድሎ ያገኘነውን ነጻነት እና ከነጻነታችን የሚመነጨውን ብሔራዊ ክብራችንን እና ማንነታችንን አጉድሎት ቆይቷል። በዓለም አቀፍ አደባባይ አንገታችንን ከማስደፋት ባለፈ ተመጽዋች /ጠባቂ አድርጎንም ቆይቷል።

ድህነት እና ኋላ ቀርነት ለብሔራዊ ክብር ትልቅ ችግር በሆነበት፤ ጠባቂነት እና ተመጽዋችነት ብሔራዊ ክብርን በሁለንተናዊ መንገድ በሚፈታተንበት በዚህ ዘመን፤ ድህነታችን እና ኋላ ቀርነታችን ብዙ ዋጋ አስከፍሎናል። ትናንቶቻችንን ብቻ ሳይሆን ዛሬን በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እንድናልፍ ፤ በነገዎቻችንን እርግጠኛ እንዳንሆን አድርጎናል።

ዛሬ ላይ፤ ድህነትን ታሪክ እናደርጋለን በሚል ሀገራዊ መነቃቃት ከዚህ ብሔራዊ ክብርን ከሚያጠለሽ ሀገራዊ ፈተና ለመውጣት እና የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር ሰፋፊ ጥረቶች እያደርን፤ በተስፋ የተሞሉ ስኬቶችን እያስመዘገብን ነው። በዚህም ነገዎቻችንን ከትናንት ይልቅ ብሩህ እና በተስፋ ተጠባቂ እየሆኑ ነው።

የእስካሁን የልማት ጉዟችን ፤ ትናንት ለነጻነታችን በቁርጠኝነት ተንቀሳቀስን ፤ ነጻነታችንን ማስከበር እና የነጻነት ተምሳሌት መሆን እንደቻልነው ሁሉ ፤ ዛሬም በተመሳሳይ መልኩ መንቀሳቀስ ከቻልን ለዘመናት ብዙ ዋጋ ያስከፈለን ድህነት እና ኋላቀርነት ከኛ አቅም በላይ ሊሆኑ እንደማይችል በተጨባጭ ማየት እንድንችል ዓይናችንን የከፈተ ነው።

ለዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለፉት ሦስት ዓመታት እውቅና ያገኘንባቸው በተለይም በግብርናው ዘርፍ የበጋ የመስኖ የስንዴ ልማትን ጨምሮ በሩዝ ልማት ፤ በሌማት ትሩፋት እና በኩታ ገጠም እርሻ እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶች፤ በተለይም በምግብ እህል ያሉብንን ጠባቂነት መሻገር የሚያስችል ጅማሬ ላይ ስለመሆናችን ማሳያ ነው።

የአንድነታችንና ብሔራዊ ክብራችን አንዱ መገለጫ የሆነውን የዓባይን ግድብ፤ ከውስጥ እና ከውጪ ፈተናዎች ታድገን ለፍጻሜ ያደረስንበት ቁርጠኝነት ፤ በቱሪዝም ዘርፍ በገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ያሉ እና የተገነቡ ፕሮጀክቶች ፤ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማነቃቃት ኢትዮጵያ ታምርት በሚል መሪ ቃል እየሄድንበት ያለው የመነቃቃት ጉዞ፤ በልማት ብሔራዊ ክብራችንን ሙሉ ለማድረግ የጀመርነው ጥረት ስኬት ማሳያ ናቸው።

ባለንበት ዘመን ድህነትን እና ኋላቀርነትን ተሸክሞ፤ እነሱ በሚፈጥሩት ፈተና ጎብጦ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተሰሚነትን በመፍጠር ብሔራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ የሚቻል አይደለም። ብሄራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ በኢኮኖሚ አቅም መግዘፍ እና ከጠባቂነት መውጣት፤ ለዚህ የሚሆን ብሔራዊ መነቃቃት መፍጠር የግድ ነው።

በርግጥ ሕዝባችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ድህነት እና ኋላ ቀርነት የብሔራዊ ክብራችን ተግዳሮት እንደሆነ ተረድቶ ይኸንን ለመሻገር ከፍ ባለ መነቃቃት እየተንቀሳቀስን ያለበት ወቅት ነው ። ለዚህም ሀገራችን በብዙ አስቸጋሪ ፈተናዎች ውስጥ በነበረችባቸው ወቅቶች ሳይቀር ያስመዘገበችው እና እያስመዘገበች ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ተጨባጭ ማሳያ ነው።

አሁናዊ የልማት መነቃቃታችን እንደሀገር ብሔራዊ ክብራችንን ሙሉ ከማድረግ ባለፈ ከህልውናችን ጋር የተያያዘ ነው፤ የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄም ነው። ድህነት እና ኋላቀርነት ሊፈጥሩት ከሚችሉት ጫና እና ጫናው እንደሀገር ሊያመጣ ከሚችለው ውስብስብ ችግሮች ራስን የማሻገር ወይም በችግሮቹ ተጠላልፎ የመውደቅ ምርጫ ነው።

ለዚህም ነው በዘመናት መካከል ውድቀታችን የሚሹ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ ሌሎች ኃይሎች ልማታችንን ለማስተጓጎል ሌት ተቀን የሚሠሩት፤ ያላቸውን አቅም በሙሉ ተጠቅመው ከልማት ጉዟችን ሊያስተጓጉሉን እየተጉ ያሉት። እኛም ከልማታችን ላይ ዓይናችንን ሳናናሳ ሴራቸውን እና የጥፋት ተልእኳቸውን ለማክሸፍ በቁርጠኝነት የምንሠራው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የእርሷ ነገር - “ጠብ ያለሽ በዳቦ”

ወጋሶ

ደብዳቤ ማርቀቁን የተካነችበት የዓመታት ሥራዋ ከሆነ ከራርሟል። የብዙዎቹ ደብዳቤዎቿ ይዘቶችም ኡኡታ! የሞላባቸው ናቸው፣ በደብዳቤዎቿ ግርጌ ያሉ ዓረፍተ ነገሮች ደግሞ “ከኡኡታዬ ጋር አብራችሁኝ ሁኑ” የሚል መልዕክት ያዘሉ ተማጽኖዎች ናቸው። ይህች ሀገር አፍሪካዊ ማንነትን ወደጎን የጣለች ከመሆኗ በላይ ብትችል በዋናነት ኢትዮጵያን ከፍ ሲልም ምሥራቅ አፍሪካን ለማባላት በመጣጣር ላይ የምትገኝ ነች።

ይህች ሀገር፣ ታላቋን ሀገር ኢትዮጵያን የምትፈታተናት ለምን እንደሆነ ከብዙዎቹ የተደበቀ ምስጢር እንዳልሆነ አስባለሁ። ከዘመናት በፊት ሲያባንናት የነበረው የዓባይ ወንዝ ጉዳይ ነበር ፣ ዛሬም ድረስ ሲያስበረግጋት የሰነበተው ይኸው ታላቁ ወንዝ ዓባይ ነው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት ማለትም በአራተኛ ምዕተ ዓመት የነበረ አንድ ፋላስፋ፤ ግብጽ የናይል ስጦታ እንደሆነችና ‘ናይልን የተቆጣጠረ ሁሉ ግብጽን በእጁ እንዳደረገ ይቆጠራል’ በማለቱ ፤ ግብጻውያን ገዥዎች ይህንን ቅዠት ተግባራዊ ለማድረግ ለዘመናት ሲሯሯጡ ኖረዋል። የተባሉትን ያንኑ ተረት የሙጥኝ ብለው ዛሬም ድረስ ተጣብቀውበት ቀርተዋል።

በዚህ ባፈጀ አባባል ከመወረሳቸው የተነሳ ሁሌም ሕልማቸው የዓባይን ምንጭ መቆጣጠር ነው ፣ እሱ የማይሳካላቸው ከሆነ ደግሞ የዓባይ ወንዝ አመንጪ የሆነችውን ኢትዮጵያን ማተራመስ የዘወትር እቅዳቸው አድርገው ዘልቀዋል። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለመሥራት የመሠረት ድንጋይ መጣሏን ባስተዋሉ ጊዜ ሀገራችንን በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካና በሰላሙ ዙሪያ ለማዳከም በብዙ ኳትነዋል፤ ወጥተዋል፤ ወርደዋል። እነሆ! በቀጥታም ሆነ በተልዕኮ ልማቷን ለማደናቀፍና ሰላሟን ለማደፍረስ ከ13 ዓመታት በላይ ተግተዋል።

ለጊዜው በተዘዋዋሪ የሚያደርጓቸውን ሴራዎች ወደጎን እንዳርግና በቀጥታ ሲያደርጉ የነበረውን የከፋት ጥግ እናስታውስ። ለአብነት ያህል ኢትዮጵያ ገና ግድቡን በጀመረችበት አካባቢ የወንዙን አቅጣጫ መቀየሩን ሲሰሙ “ኡ!ኡ!..” አሉ፤ ትንሽ ቆይቶ ደግሞ ግድቡ የመጀመሪያውን ዙሩ ውሃ መያዝ ጀመረ ሲባል፣ “ያዙኝ! ልቀቁኝ!” ሲሉ ተደመጡ።

በየዓመቱ ሁለተኛውና ሶስተኛው ዙር ውሃ መያዙን ሲሰሙ “እሪ!” በማለት የድረሱልኝ ጥሪ አሰሙ። ሁለቱ ተርባይኖች ተጠባቂውን ኃይል ማመንጨት ጀመሩ በተባሉ ጊዜ ደግሞ “ወይኔ! ጉዴ ፈላ!” ሲሉ አምቧረቁ። ከሳቸውን ይዘው በመሮጥ አብረዋቸው የሚጮኹላቸውን ፈለጉ፤ በዚያም አልሰምር ሲላቸው ኢትዮጵያውያኑን አንዱን በአንዱ ላይ በማነሳሳት ማፋጀትን አማራጭ አደረጉ።

እርግጥ በዚህ ሁሉ ፈተና ውስጥ ሀገራችን ኢትዮጵያ ምንም አይነት ጉዳት አልደረሰባትም ማለት አይቻልም። በተለይ ግብጽ በተልዕኮ በምታደርገው ኢትዮጵያን የማተራመስ ስልት፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሰምሮላታል ማለት ያስደፍራል። ለበርካታ ዓመታት እርስ በእርስ እንድንፋጅ የተለያየ ርዕስ እየሰጠችን በብዙ ፈትናናለች፤ አጀንዳ ከመስጠት ባሻገር ፤ ባንዳዎችን እስከማስታጠቅ የዘለቀ ትጋት አሳይታለች። በዓለም አቀፉ መድረክ አቁማን ልትሞግተን ጥራለች፤ “የእኔ ነው” በምትለው በአረብ ሊግ ጉያ ተሸሽጋ ጫና ለመፍጠር ደፋ ቀና ስትል ከርማለች።

ነገር ግን ለግብጽ እያንዳንዱ ርምጃ ኢትዮጵያ አንዴም ቢሆን ሽብረክ ስትል አልተስተዋለችም። ግብጽ በከፋት በትር በራችንን ደጋግማ ለማንኳኳት ብትሞክርም ሊከፈትላት አልቻለም። በዓለም አቀፍ ደረጃ ባቀረበቻቸው ተደራራቢ ክሶች ተገቢውን ምላሽ ሲሰጡ የከረሙት የኢትዮጵያ መንግሥትና ምሁራኗ ሁሌም ቢሆን ኢትዮጵያ ውሃውን መጠቀም የምትሻው ፍትሃዊነትን በተላበሰ መንገድ መሆኑንና በውሃ ሀብቱ ላይ ደግሞ ኢትዮጵያ የመጠቀም መብት እንዳላት ደጋግመው አስረግጠው ሲያብራሩላት ሰንብተዋል።

ይሁንና ግብጽ እውነታውን እያወቀች ዛሬም ቢሆን ኢትዮጵያን ከልማት ለማሰናከል በብዙ እየጣረች ትገኛለች። በተለይ ልማታችንን ተረጋግተን እንዳናሳልጥ ሰላማችንን በተዘዋዋሪ በማደፍረሱ በኩል የቻለችውን ያህል ትባዝናለች። የተለያዩ አዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮችን እየፈጠረች በሌሎች ጸረ ሰላም ኃይሎች በመታገዝ ተልዕኮዋን እያስፈጸመች ትገኛለች። ትልቁ እና ዋንኛ ዓላማዋ ደግሞ ኢትዮጵያ በምንም አይነት መንገድ በኢኮኖሚ እንዳትጠነክር፣ በፖለቲካውም እንዳይሳካላት ለማድረግ ነው። በጥቅሉ በቀጣናውም ሆነ በምስራቅ አፍሪካ ተሰሚነት እንዳይኖራት ማድረግ ነው።

የኢትዮጵያን ሰላም፣ ኢኮኖሚና ፖለቲካ ለማዳከም በተናጠል የምታደርገው እኩይ ተግባር አመርቂና አዋጭ ሆኖ ስላልታያት ደግሞ በአሁኑ ወቅት ስልቷን ቀይራ ሌላ የሴራዋ ተጋሪ የሆነ አካል በመጠቀም የተቻላትን ሁሉ በመሞከር ላይ ትገኛለች። ሰሞኑንም የተስተዋለው ጉዳይ ይኸው ነው። ግብጽ፣ አፍሪካዊነቷን አምና ለመቀበል ቋቅ ሲላት መኖሯን ዘንግታው ኢትዮጵያን መጉዳት እችላለሁ በሚል ተላላ እሳቤ ወደሶማሊያ ማቅናቷ በቀጣናው ትልቅ አጀንዳ ሆኖ መወራት ከጀመረ ቀናት ተቆጥረዋል።

ሶማሊያ፣ ሰላሟን በማረጋገጥ ረገድ እመቤቷ የሆነቻት ኢትዮጵያን ወደጎን አድርጋ ከግብጽ ጋር በአመራሮቿ አማካይነት ሽር ጉድ ስትል እንደቆየችም ተጤኗል። ግብጽ ወደ ሶማሊያ የመሄዷ ነገር ያው የሚታወቅ እኩይ ዓላማ አንግባ ነው። አሯሩጦ የወሰዳት ነገር ወዲህ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፍጻሜውን ያገኛል፤ ተጨማሪ ኃይልም ያመነጫል መባሉ አንዱ ነው፣ ወዲያ ደግሞ ሀገራችን ከራስ ገዟ ሱማሊላንድ ጋር የባህር በር ለማግኘት የሚያስችላትን ስምምነት መፈራረሟ እና እሱ እውን ከሆነ “አበቃልኝ በቃ” በሚል ፍራት አቅል አሳቷት ነው።

ኢትዮጵያን ከልማቷ ለማናጠብ በራሷ ወጥታ ወርዳ ያቃታትን ሴራ በሌሎች ለመጠቀም እየሞከረች ነው። ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ወደ ሞቃዲሾ አየር ማረፊያ የደረሱት የግብጽ ሁለት የጦር አውሮፕላኖች መሣሪያዎችን የጫኑ ስለመሆናቸው ተሰምቷል። ‘ጠብ ያለሽ በዳቦ…’ እንዲሉ ይህ አካሔዷ እርሷን ጨምሮ ለማንም ቢሆን የሚያዋጣ አይደለም።

የ“ጠብ ያለሽ በዳቦ” አካሔዷን ልታቆም ይገባል። እውነት ለመናገር ግብጽ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን መሆናችንን የዘነጋች ይመስላል። ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ባለቤት መሆን ከወኔ እና ቆፍጣና ልብ ጋር ሲነጻጸር ምንም እንደሆነ የእኛን ያለፈ ታሪክ ማገላበጡ ብቻ በቂ ይመስለኛል። ያውም የአንጸባራቂ ታሪክ ባለቤት ስለመሆናችን መረሳት የለበትም።

ቀጣናው በአግባቡ ሲጠበቅ የኖረው በኢትዮጵያ ቆፍጣናነት እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው። አሁንም ቢሆን በቀጣናው ለመፍጠር የተሞከረው ውጥረት የሚረግበው በእኛው በኢትዮጵያውያን ትጋት ነው። እኛ ለበርካታ ዓመታት የሶማሊያውያንን ችግር ስንፈታ፤ ሠላማቸውን ስናስጠበቅ የኖርን ነን።

ቁልፍ አጋራቸው መሆናችን ሊረሳ አይገባም። ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ጋር ሆድና ጀርባ ለመሆን የሚዳዳት ከሆነ ደግሞ መከራን በገዛ እጇ በራሷ ላይ እንደጋበዘች ይቆጠራል። ኢትዮጵያ ለሶማሊያ ደህንነት ወታደሮቿን ስትገብር ቆይታለች። ከፍ ያለ መስዋዕትነትም ከፍላለች፤ አሁንም ቢሆን ሶማሊያ የሚሻላት እውነተኛ ከሆነችው ጎረቤቷ ጋር ህብረት ማድረግ ነው። ካልሆነ ግን “በሞኝ ክንድ የእባብ ጉድጓድ ይለካል” ነውና ነገሩ ምርጫዋን ማስተካከል የእርሷ ፋንታ ነው።

የዓባይ ግድብ፣ ለቀጣናዊ ትስስር ትልቁን ድርሻ የሚይዝ እንጂ ሰላምን የሚያደፈርስ አይደለም፤ መሆን የለበትምም። ኢትዮጵያ ከግድቡ ጋር በተያያዘ የሚመጡባትን ጫናዎች መቋቋም የምትሻው ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም መርህን መመሪያዋ በማድረግ ነው።

ወትሮም ቢሆን ኢትዮጵያ ዓባይን በትብብር ላይ ተመስርተን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንጠቀምበት እንጂ ለብቻዬን ልያዘው አላለችም። የውሃ ሀብት ክፍል አጠቃቀማችን ፍትሃዊና ምክንያታዊ መሆን ከቻለ ደግሞ ቀጣናውን ጨምሮ ለሌሎች የሚተርፍ ልማትን ማካሔድ ያስችለናል። ከዚህ በተረፈ የግብጽን ጉዳይ በማስታመም ብቻ መዝለቅ ለሌላ ድፍረት እንድትበረታታ የማድረግ ያህል ነውና ቦታዋን እንድታውቅ ማድረጉ ተገቢ ነው እላለሁ።

# ወቅታዊ

# “ያለፈው ዓመት ችግሮቻችን መንስዔ እኛ ከሆንን ዘንድሮ የመፍትሔው አካል መሆን ያለብን እኛው ነን”

ዶክተር አለምሰገድ ደበሌ
በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር

አስቴር ኤልያስ

ኢትዮጵያውያኑ አሮጌውን ዓመት ተሻግረው የሚቀበሉት አዲስ ዓመትን ብቻ አይደለም፤ በዓመቱ መጨረሻ ወራት ውስጥ በሚዘንበው ዝናብ ምድር ረስርሳ የምትሰጠውን የመስከረም ወር አዝመራ እንዲሁም በዓመት ዞሮ የሚመጣውን ዓደይ አበባንም ጭምር ነው። በተለይም ሐምሌ እና ነሐሴ ወር ላይ እየደነፋ የሚያልፈው ወንዝ ጠርቶ፣ መስኩም በአበባ አጊጦ ስለሚታይ በየሰው ልብ ውስጥም ብሩህ ተስፋ መፈንጠቅ የሚጀምርበት ጊዜ ነው።

አሮጌውን ዓመት ከነበረው ጭንቀት ጋር ወዲያ በመጣል፤ እንደየአቅም መጠን በአዲስ ዓመት በአዲስ ተስፋ ለመኖር መስከረም ሲጠባ አንድ ተብሎ ኑሮ በአዲስ መልክ ይጀመራል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተጠናቀቀው ዓመት ችግር ሆነው የቆዩ ጉዳዮች በአዲሱ ዓመት ደግመው እንዳይከሰቱ መፍትሔው ምንድን ነው? አዲሱን ዓመት በምን አይነት ስነ ልቦና መቀበልስ ያሻል? በተለይ በአሮጌው ዓመት የታጣው ሰላም ዘንድሮ እንዴት መታደስ ይችላል በሚሉና በመሰል ጥያቄዎች ዙሪያ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ መምህር ከሆኑትና ብዙ ጊዜ በሰላም ዙሪያ ከሰሩ አለምሰገድ ደበሌ (ዶ/ር) ጋር አዲስ ዘመን ቃለ ምልልስ አካሂዷል። እንደሚከተለውም ቀርቧል።

**አዲስ ዘመን፡- 2016 ዓ.ም እንደ ሀገር እንዴት ይታያል ?**

**አለምሰገድ (ዶ/ር)፡-** በተጠናቀቀው በ2016 ዓ.ም በርካታ መልካም የሆኑ ስራዎች ተሰርተዋል። ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ እንደ አገር ፈታኝ የሆኑ ነገሮችም ነበሩ። ከተከናወኑ የተሻሉ ተግባራት ውስጥ መንግስት በተለይ በኢኮኖሚው ዘርፍ የወሰዳቸው ማሻሻያዎች የሚጠቀሱ ናቸው። ፋይዳው ምንድን ነው? ተብሎ የሚጠየቅ ከሆነ ደግሞ በሂደት የሚታይ ይሆናል የሚል ምላሽ አለኝ።

ሌላው መንግስት ዲፕሎማሲው ላይ ጥሩ ሰርቷል የሚል አተያይ አለኝ። ከዚህ ከዲፕሎማሲው ጋር ተያይዞ እንደ አገር በመልካም ሁኔታ የተንቀሳቀስን ይመስለኛል። በተለይ ከምዕራባውያን፣ ከአሜሪካ፣ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያለንን ክፍተት በጥሩ ዲፕሎማሲያዊ አካሔድ የሞላን ይመስለኛል። ከዚህም የተነሳ ወሳኝ የሆኑ ተቋማት እርዳታም ብድርም ለመስጠት መወሰናቸው በተፈጠረው መልካም የሆነ ዲፕሎማሲ አማካይነት ነው የሚል እምነት አለኝ።

በአንጻሩ ደግሞ እንደሚታወቀው ሲፈትነን የቆየው የሰላም መታጣት ሁኔታ ነው። በእርግጥ ሰላም እንዲሰፍን ብዙ ጥረት ተደርጓል። ይህም ጥረት በመንግስት፣ በኃይማኖት አባቶች፣ በአገር ሽማግሌዎችና በተለያዩ አካላት እየተደረገ ነው። እኔ በበኩሌ በሰላም ዙሪያ የተወሰኑ ስራዎችን ስሰራ ቆይቻለሁ። በእንዲህ አይነት መልኩ ጥረቱ ቢኖርም ስኬቱ ላይ ግን ያን ያህል ለውጥ አልታየም።

አሁንም ቢሆን እዚህ እና እዚያ የሚታዩ ውጥረቶች አሉ። ባለፉት ጊዜያት ፈታኝ ሆኖ የሰነበተው የሰላም መታጣቱ ጉዳይ እስከ ዓመቱ መጨረሻ አሳሳቢ ሆኖ ዘልቋል። በተለይ ከአዲስ አበባ ውጭ ባሉ አካባቢዎች እንደልብ ማምረት እንዳይቻልና ኢንቨስት እንዳይደረግ የሚያግድ ሁኔታ ተስተውሎ ከርሟል።

ሌላው በአሮጌው ዓመት ሲያስጨንቀን የነበረው የኑሮ ውድነቱ ነው። በእርግጥ የኑሮ ውድነቱ በኢትዮጵያ ብቻ የተከሰተ ተዓምር ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም የኑሮ ውድነቱ ዓለም አቀፋዊ ነው። እኛ ዘንድ ደግሞ ከጊዜ ወደ ጊዜ የኑሮ ሁኔታው ሲያሻቅብ ይታያል። እሱ ደግሞ ሕዝቡን ሲፈትነው ከርሟል። በእኔ እይታ እነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች ፈታኝ ነበሩ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መጥፎ ነው ከምንለው ከትናንቱ ታሪካችን መማር የምንችለው እንዴት ነው?**

**አለምሰገድ (ዶ/ር)፡-** ከአጭሩም ሆነ ከረጅሙ ታሪክ የምንማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ታሪክ ራሱ ትምህርት ቤት ነው። የሚያስተምረው ነገር አለው። ትልቁ ነገር ከጥሩውም ሆነ ከመጥፎው ነገር ትምህርት መውሰድ መቻል ነው። ጥሩነቱ ጥሩውን ነገር ለመቀጠል የሚስችል መሆኑ ነው። ለምሳሌ ዲፕሎማሲ ላይ የተሰራው አይነት በጎ ተግባር መማርና ለቀጣዩም ዓመት የበለጠ ጠንክረን ለመስራት መጣር ነው። የስራ አጥ ቁጥሩን ለመቀነስ የተወሰኑ መልካም ተግባራት ተሳክተዋል። እነዚያን የበለጠ ማጎልበት ወሳኝ ነው።

ነገር ግን እንዳይደገም ማድረግ ያለብን መጥፎውን ታሪክ ነው። ስለዚህ ከመጥፎ ታሪክ መማር ያለብን ደግመን ላለመስራት ስንጥር ነው። በተቻለ መጠን ሁሉ መጥፎውን ታሪክ ለማስቀረት መስራት ነው። ዋናው ጥያቄ የሚሆነው ምን ያህል እንማራለን የሚለው ነው። የምንቀየረውም ለውጥም ማምጣት የምንችለው በተማርነው ልክ ነው። ከመጥፎው ታሪካችን ብዙ መማር ከቻልን በብዙ መንገድ እንቀየራለን። በመቀየራችንም ብዙ ለውጥ በሕይወታችን ላይ እናመጣለን። በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ይህ እንደ ማኅበረሰብም እንደዚያው ብዙ ለውጥ ማስመዝገብ ይቻላል።

ባሉብን ችግሮች ላይ ተወያይተን ችግራችንን የምናልፍበትን መንገድ መፈለግ ነው። ይህ ደግሞ ለአንድ አካል ወይም ማኅበረሰብ የሚተው ሳይሆን አሊያም ደግሞ ለመንግስት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉም ድርሻ መሆኑን መረዳቱ ተገቢ ነው። ከታጠቁ ቡድኖች ጋር ውይይት አድርጎ በተለይ በሰላሙ ዙሪያ መምከሩ ወሳኝ ነው። መስማማት የሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ መምከርና የተራራቀውን አካል ለማቀራረብ መጣር መልካም ነው የሚል አተያይ አለኝ። በዚህ ውስጥ ሁሉም የየራሱን ፍላጎት ከመለጠጥ ይልቅ ጠበብ ማድረግ የሚጠበቅበት ይመስለኛል። በዚህ ውስጥ መጥፎ ታሪክ የምንለውን ጉዳይ ወደጥሩ መቀየር ይቻላል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- አዲስ ዓመትና አዲስ ተስፋ የሚያገናኛቸው ምንድን ነው? አንድ ሰው እቅድ ማቀድ ያለበት አዲስ ዓመትን ብቻ ጠብቆ መሆን አለበት?**

**አለምሰገድ (ዶ/ር)፡-** አዲስ ዓመትና ተስፋ ሁለቱም አዲስ ናቸው። የሰውን ልጅ የሚያኖረው በተስፋ ነው። የሰው ልጅ ተስፋ የቆረጠ ዕለት የሚሞተው በቁሙ ነው። ስለሆነም ተስፋ ሁልጊዜ መኖር አለበት። ነገር ግን ጊዜያት የሚለኩት በወራት፣ በዓመታት ስለሆነ ምናልባት ከአምናው የተሳካልን ነገር ሲኖር እቅዱም የግድ ያስፈልጋል።

በእርግጥ እቅድ የሚታቀደው በአዲስ ዓመት ብቻ አይደለም። እቅዱ በሚያስፈልግበት ሰዓትና እንደተቋምም ካሰብነው የሶስት፣ የስድስት፣ የዘጠኝ ወርና የዓመት እቅዶች አሉና የሚታቀደው በዚያ ውስጥ ነው። የአጭርና የረጅም ጊዜ እቅዶች አሉ። ግን መሆን ያለበት እቅድ እንኳ ባይኖረን በአዕምሮ መዘጋጀት ያስፈልገናል። ወዴት እና እንዴት ነው የምንሔደው የሚለውን ለማሰላሰል ይጠቅመናል፤ በአዕምሮአችን የምናወጣውና የምናወርደው ሐሳብ እንደ ዝግጅት የመሚቆጠር ነውና ወደ እቅድ ለመቀቀየር ይረዳናል።

እቅዳችንን በተቻለ መጠን ሳይንሱ እንደሚለው የተሻለ ማድረግ ነው። በጣም አጭር የሆነ፣ ሊተገበር የሚችል፣ የሚመዘን፣ የሚታይ አድርገን ማቀዱ አዋጭ ነው። እቅድን በጣም ለጥጦ ማቀድ ተግባራዊ እንዳይሆን ሊያደርገው ይችላል። አዲስ ዓመት ሲመጣ የሰው ልጅ ያስባል፤ ከአምናው ዘንድሮ የተሻለ ነገር አገኛለሁ ብሎ ተስፋ ስለሚያደርግ ይዞለት የሚመጣው ተስፋን ነው።



በተለይ በእኛ አገር ደግሞ ወቅቶቹ ራሳቸው ያንን የሚያመለክቱ ናቸው። ደረቅ ከሆነው በጋ፤ እርጥብ ወደሆነው ክረምት ገብተን ልክ መስከረምና ጥቅምት ላይ ደግሞ አረንጓዴ ነገሮችን የምናይበት ነውና በተስፋ እንሞላለን። እቅዶችን የምናቀድው በዚህ ተስፋ ውስጥ ሆነን ነው። በዓመቱ መጀመሪያ ሰዎች የሚያቅዱትም ለዚያ ነው። እቅድ በተከታታይ በአጭር ጊዜና በረጅም ጊዜ ተብሎ መታቀድ ያለበት ሲሆን፣ እቅዱ ውስጥም ተስፋ መኖሩን አመላካች ነው። የሰው ልጅ ደግሞ የሚኖረውም ተስፋውን ነው። የሰው ልጅ ወደ ስኬት የሚቀይረውም ያንኑ ተስፋውን ነው። አዲስ ዓመትና ተስፋ የሚያያዙት ለዚያም ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙ ሰዎች በአዲስ ዓመት እቅድ ያቅዳሉ፤ ከሚታቀዱ እቅዶች መካከል ብዙዎቹ ራሳቸውን ከሱስ ወጥመድ ለማላቀቅ ነው፤ ከዚህ ባለፈ ግን ለተሻለ ነገ የሚያስፈልገን የስነ ልቦና ዝግጅት ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**አለምሰገድ (ዶ/ር)፡-** ሰዎች የሚያቅዱት እንደየፍላጎታቸው ነው። ከሱስ መላቀቅ አለብኝ ብሎ የሚያቅደውም ሰው ዋናው ችግሩ ሱስ ነው ማለት ነው። የሌሎችም ሰዎች ችግር እንደዚያው የተለያየ ነው። ገንዘብ የሚያባክን ሰው ከሆነ ደግሞ ገንዘቡን እንዴት በቁጠባ መጠቀም እንዳለበት እቅድ ያወጣል። እኛ እንደ አገር ያሉብን ችግር ምንድን ነው? ማቀድ ያለብን እዛ ላይ ነው። እና በአጠቃላይ ችግሮቻችንን አይተን ነው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ወቅታዊ

# “ያለፈው ዓመት ችግሮቻችን መንስዔ እኛ ከሆንን...

ከገጽ 6 የዞረ

እቅዶቻችንን የምናቅደው።

ሌላው ደግሞ ችግሮቻችን ላይ ብቻ ሳይሆን ጥሩ ነገሮቻችንም ላይ እቅድ ማቀድ ያስፈልጋል። አምና የተሳካልንን ስኬት ዘንድሮ በአዲሱ ዓመትም ለመድገም እቅድ አስፈላጊ ነው። ከዚህ የተነሳ እቅዶቻችንን ስኬታማ ለማድረግ የስነ ልቦና ዝግጅት ያስፈልጋል። ለምሳሌ ያቀድኩት እቅድ ባይፈጸም አማራጭ ብለን የምንይዘው ነገር ይኖራል። ስለዚህ እቅዶቻችንን ስናቅድ አጋጣሚ ሆኖ ባይሳካ ተለዋጭ እቅድ ሊኖረን ይገባል። በስነ ልቦናም ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል። ያቀድነው ባይሳካ በተለዋጭ በያዝኩት እቅድ እዴት ማሳካት እችላለሁ የሚለው መጤን ይኖርበታለል። ያልተጠበቁ ነገሮች ቢከሰቱብን ያንን ነገር እንዴት መመለስ እንችላለን በሚል በስነ ልቦና ረገድ መዘጋጀት ይኖርብናል። ስለዚህ እዛ ላይ መስራትና መወያየት ያስፈልጋል። ከዚህ የተነሳ የአዕምሮ ዝግጅት ወሳኝ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን ስትራቴጂም ያስፈልጋል። እቅዱን ለማሳካት መከተል ያለብኝ ስትራቴጂ ምንድን ነው? የሚለውን መገንዘብ ወሳኝ ነው። ለምሳሌ የአጭር ጊዜ እቅዴ እንዲሳካልኝ መከተል ያለብኝ ስትራቴጂ ምን አይነት ነው? የምከተላቸው ስትራቴጂዎችስ በትክክል እቅዴን ማስፈጸም የሚችሉ ናቸው? የሚለውን መረዳት ተገቢ ነው። ‘መጥፎ ነገር ቢከሰት በዚህ በዚህ ስትራቴጂ ልወጣው እችላለሁ’ የሚል የስነ ልቦና ዝግጅት መኖር አስፈላጊ ነው። የስነ ልቦና ዝግጅት ካለ ለሚመጣው ችግር ሁሉ ቅድመ ዝግጅት ስለሚኖር በማማከር አሊያም በራስ በመተማመን ችግሩን መሻገርና ለአዲስ ተስፋ መዘጋጀት የሚያስችል ይሆናል። ከራስ የተሻለ አካል ካለ ደግሞ ካለፉበት መንገድ ትምህርት ለመውሰድም በቂ ማንነት ስለሚኖረን የሚገዳደር ነገር አይኖርም።

እንደ አገር ከሆነ ደግሞ የምናስበው፤ እንደ አገር የምናሳካቸውን ነገሮች ለማሳካት ማቀድ ነው። ተሳክቶልን ከሆነ ደግሞ እሰየው ነው። ካልተሳካልን በአዲስ መንፈስ ለቀጣዩ መዘጋጀት ነው። አገር ማለት የመሪዎች ስብስብና ሕዝብ አንድ ላይ የሚኖርበት ስፍራ ነው። ስለዚህ ልምድ የምንቀስመው ከዚያ ነው። ወደ ማኅበረሰባችንም ተመልሰን ልምድ መውሰድ ያስፈልጋል። የተሻሉ አገራትም እቅዶቻቸውን እንዴት እንዳሳኩም ልምድ መውሰድ ብልህነት ነው። በተለይ ደግሞ ከእኛ አገር ጋር ተቀራራቢ የሆነ ነገር ካላቸው አገራት ልምድ መውሰዱ ተገቢ ነው ባይ ነኝ።

በስነ ልቦና ደረጃ ጠንካራ መሆን ብቻ ሳይሆን በፋይናንስ ደረጃ ጠንካራ መሆንም የግድ ይላል። አንዳንድ ትልልቅ ፕሮጀክቶችን በአገር ደረጃ ለማከናወን ሲታቀዱ በገንዘብ በኩል መዘጋጀትም የግድ ነው። ምክንያቱም አንድም ትልልቅ ፕሮጀክቶች ታቅደው ስኬታማ መሆን የማይችሉትና የሚከሸፉት ከፋይናንስ እጥረት የተነሳ ነው። ስለሆነም ፋይናንሱን እንዴት ማስተዳደር ይቻላል? የሚለው ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል። ለታቀደው እቅድ እንዴት መዋል ይችላል የሚለው በአግባቡ መጤን ይኖርበታል። በዚህ ደረጃም አጥብቆ መስራት ያስፈልጋል ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያን በተጠናቀቀው በ2016 ዓ.ም ያጋጠማት ብዙ ስብራት መኖሩ ይታወቃል፤ እነዚያ ስብራቶች በ2017 ዓ.ም እንዳይደገሙ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አስምሰገድ (ዶ/ር)፡-** ያለፈው ዓመት ችግሮቻችን መንስዔ እኛ ከሆንን ዘንድሮ እንዳይደገም የመፍትሔውም አካል መሆን ያለብን እኛው ነን፡ ስለዚህ በቀጣይ ችግሩ የበለጠ እንዳይፈትነን ለመፍትሔው መጣር ነው። እኔ መምህር ነኝ። በመመምህርነቴ ማድረግ የምችለው ማስተማር ነው። ለችግሩ መፍትሔ ለማበጀት ስምምነት ላይ መድረስ የግድ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሁሉም በአንድ አይነት ሀሳብ ሊስማማ አይችልም። ስለዚህም በማያስማሙን ነገሮች ላለመስማማት መስማማትም ያስፈልጋል።

በአሁኑ ወቅት እንኳን በአንድ አገር ውስጥ ያለን ዜጎች ቀርተን በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው ማኅበረሰብ እንኳ በብዙ ጉዳዮች ወደስምምነት እየመጡ ያለበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ስለዚህም ማሰብ የሚኖርብን እንደዛ ነው። በተቻለን መጠን ያሉንን ልዩነቶች ከልብ ተወያይተን ስምምነት ላይ መድረስ ወሳኝ ነው። ውይይት ሲባል እንዲሁ ለይስሙላ የሚደረግ መሆን የለበትም። አምነንበትና ይበጀኛል ብለን የምናደርገው መሆን አለበት። ዋናው ነገር የችግሩን ጭብጥ ማወቅ ነው። ችግሩን በትክክል ከተረዳነው ለዚያ ችግር መፍትሔ መፈለግ ነው። የችግራችን ጊዜ የቱንም ያህል የረዘመ ቢሆንም መፍትሔ አይታጣለትም።

እርግጥ ነው ጊዜ ሊወስድ ይችል ይሆናል፤ ምናልባትም በአንድ ወር አሊያም በአንድ ዓመትም ላይፈታ ይችል ይሆናል። በረጅም ጊዜ ሂደት ውስጥም ቢሆን ችግሮችን ለመፍታት የመፍትሔ አካል ለመሆን መዘጋጀት ትልቁ ጉዳይ ይሆናል። ወደ መፍትሔው ለመምጣት መረጋጋት በራሱ አንድ ጉዳይ ነው።

በሁሉም አቅጣጫ ብዙ ልናጣቸው የምንችላቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። እንደዚያ እንኳ ቢሆን ለአገር ሰላም ሲባል ልብን ማስፋት ተገቢነቱ አጠያያቂ አይሆንም እላለሁ። በውይይት ደግሞ የማይፈታ ነገር አይኖርም፤ በመነጋገር ውስጥ መፍትሔ አይጠፋም። ስንወያይ ግን እውነትነት ባለው አካሔድ መሆን አለበት።

ከዚህ ውጭ ዝም ብለን ዓመቱን ሙሉ ተሰብስበን ፋይዳ የሌለው ውይይት አድርገን መመለስ አይነት ከሆነ ትርጉም አይኖረውም። እሱ በጊዜ፣ በገንዘብና በጉልበት መቀለድ ነው። እንደዚያ ከሆነ የምንፈልገውን ለውጥ ማምጣት፤ አንዳች ስምምነት ላይም መድረስ አንችልም። የምንናፍቀው ሰላምም በተግባር መሬት ላይ ወርዶ ማየት አንችልም።

እኔ ሁሌ የሰላም ጉዳይ ያሳስበኛል፤ በአሁኑ ወቅት የምንሰማውና የምናስተውለው ነገር እየከበደ መጥቷል። ከዚህ በኋላ ባሳለፍነው አይነት መንገድ ማለፍ አንፈልግም፤ ሰላም መሰረታዊ የሆነ ነገር ነው፤ ሰላም ካለ ቋጠሮው ሁሉ ይፈታል። ከባዱ ነገር ሁሉ ቀላል ይሆናል። ለሁሉ ነገር መሰረቱ ሰላም ነው። ሰላም ሲኖር ልማት አይስተጓጎልም፤ ምርታማነት ይጨምራል። ምርታማነት ጨመረ ማለት ደግሞ በኑሮ ውድነት የጎበጡ ወገቦች ቀና ይላሉ።

ትልቁ ነገር ሰው የመንቀሳቀስ፣ የማልማትና የማምረት ነጻነት እንዲኖረው በሰላሙ ዙሪያ አበክሮ መስራት ነው። አንዱ እዚህ አገር ላይ ችግር የሚፈጥርብን እና የሚያጋጨን የኢኮኖሚ ችግር ነው። ሁሉም ሰው የተሻለ ነገር ቢኖረው ከዚያም የተነሳ የተሻለ ኑሮ ቢመራና ገቢውም እያደር የተሻለ ቢሆን አሁን እየፈተነን ያለው ችግር በጣም ይቀንሳል። እያስቸገረን ያለው የሰላም እጦት በዚህ ልክ አይገዳደረንም። ስለሆነም እዚህ ላይ እንደምንም በማለት በጣም በጥልቀት መስራት ያስፈልገናል፤ እኔ ማለት የምችለው ይህንን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአዲሱ ዓመት በተለይ ኢትዮጵያ ምርታማ የሆነች እና ሰላም የሰፈነባት አገር እንድትሆን ከሕዝብና መንግስት ይጠበቃል? ቁርጠኛ መሆን የሚጠበቅባቸውስ በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ነው? ቁርጠኝነታቸውስ የት ድረስ መሆን አለበት ይላሉ?**

**አስምሰገድ (ዶ/ር)፡-** ሰላምን የማስፈን ስራ ለመንግስት ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም። አሊያም ደግሞ በአንድ አካል ጫንቃ ላይ ብቻ የሚጣል አይሆንም። ሕዝቡም ቢሆን ሰላም ፈላጊነቱን በተግባር ማንጸባረቅ መቻል ይኖርበታል። ጠብመንጃ ያነሱትንና ችግር የሚፈጥሩትን አካላትን በሚቻለው መንገድ ሁሉ ወደ ሰላም መድረክ እንዲመጡ እና እንዲወያዩ መጋበዝ ነው።

በአሁኑ ወቅት ነፍጥ አንግተው ከኅብረተሰቡ መካከል ያፈነገጡ አካላት የወጡት ወይም የመጡት ከሌላ አገር አይደለም። የወጡት ከእኛው ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ስለሆነም ከአብራኩ የወጡትን አካላት ራሱ ማኅብረሰቡ ጣልቃ ገብቶ “ሃይ” ሊል እንዲሁም ለሰላም እጃቸውን ዘርግተው የወጡበትን ማኅበረሰቡን እንዲቀላቀሉ ማድረግ ይጠበቃል።

በእርግጥ ለእንደዚህ አይነት ችግር ፖለቲካዊ



ደረቅ ከሆነው በጋ፤ እርጥብ ወደሆነው ክረምት ገብተን ልክ መስከረምና ጥቅምት ላይ ደግሞ አረንጓዴ ነገሮችን የምናይበት ነውና በተስፋ እንሞላለን። እቅዶችን የምናቀድው በዚህ ተስፋ ውስጥ ሆነን ነው

መፍትሔም የግድ የሚል እንደሆነ አምናለሁ። ስለሆነም በመንግስትም በኩል ፖለቲካዊ የሆነ መፍትሔ ለመስጠትና ለሰላም ቁርጠኛ መሆን የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ ዝግጅት አስፈላጊ ነው። በእርግጥ በአሁኑ ወቅት ጥሪዎች በመደረግ ላይ ናቸው። እነዚያን ጥሪዎች እንዳስተዋልነው በአገር ውስጥም ሆነ በውጪውም ማወያየት ተጀምሯል። ማወያየት በራሱ አንድ ትልቅ ጅማሮ ነው። ያንን ደግሞ እንደምንም በማለት ወደፍጻሜው ማምጣት ወሳኝ ነው። ከአሁን በፊት የፕሪቶሪያው ስምምነት እንደተደረገው አይነት በዛ መልኩ ተንቀሳቅሶ ሰላምን ለማምጣት መሞከር በጣም አስፈላጊ ነው።

ሰላም እንደሚታወቅ ከግለሰብ የሚጀምር ነው። በአንድ ሰው አዕምሮ ውስጥ ሊፈጠር የሚችል ነው። ሰላማዊ የሆነ አዕምሮ ያለው ሰው የአገር ሰላምን ማምጣት ይችላል። ደግሞም ትክክለኛ የፖለቲካ መፍትሔ ለሚሹት ጉዳዮች ትክክለኛውን ፖለቲካዊ መፍትሔ መስጠት ወሳኝ ነው፤ እሱ ሲደረግ ከልብ የሆነ ምላሽ በመስጠት ጭምር መሆን አለበት። እንዲህ ሲሆን ብዙ ሊታጣ የሚችል ነገር ሊኖር እንደሚችል ማጤኑ ተገቢ ነው። እነዚህ ሁሉ ተግባራት በአንድ ጊዜ የሚከናወኑ ነገሮች አይደሉም፤ ረጅም ሒደትን የሚከተል ሊሆን ይችላልና ማኅበረሰቡም በዚያ መልክ መዘጋጀት ይኖርበታል። ከንግግር ያለፈ ዝግጅት ከሕዝቡ የሚጠበቅ ይሆናል። ሰላም የሚመጣ ከሆነ ሁሉም ነገር ሰላሙን ተከትሎ የሚመጣ ይሆናል የሚል አመለካከት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡-በእርስዎ አተያይ ኢትዮጵያን የፈተናት ልጓም ሊበጅለት ይገባዋል የሚሉት ጉዳይ ምንድን ነው? ምን አይነትስ መፍትሔ ይሰጠው ይላሉ?**

**አስምሰገድ (ዶ/ር)፡-** አስቀድሜ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ትልቁ ነገር የሰላሙ ጉዳይ ነው። ሁለተኛው የኑሮ ውድነቱ ነው። በእርግጥ መንግስትም የሚችለውን እያደረገ ድጎማ የሚያስፈልጋቸውን እንደ ነዳጅ አይነቱን እየደጎመ ይገኛል።

ከሰላሙ አንጻር እንደሚታወቀው ሁሉም ሕዝብ ሰላም ፈላጊ ነው። በተመሳሳይ መንግስትም ሰላም ፈላጊ ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የኢትዮጵያ ተግዳሮት ሆኖ የሰነበተውን የሰላም እጦትን መላ ለማለት ወደ ውይይቱ መምጣት መልካም ነው እላለሁ። ለዚህ ደግሞ በአሁን ወቅት በመንቀሳቀስ ላይ በሚገኘው ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽኑ መድረክ መጠቀምና መወያየቱ አንዱ መፍትሔ ነው ብዬ አስባለሁ። በምንችለው አቅም ሁሉ ሰላምን ማምጣት የሚችሉ ጉዳዮች ላይ መስራት ነው። በሶስተኛ ወገንም ቢሆን በአገር ደረጃ ሽማግሌዎችንና የኃይማኖት አባቶችን በመጋበዝም ጭምር መስራት ወሳኝ ነው። ሰላምን ለማምጣት መሰልቸት አያስፈልግም፤ ብዙ መድከም የሚጠይቅ ቢሆንም ከብዙ ድካም በኋላ ለውጥ ይገኛል የሚል ተስፋ ሰንቆ ለስኬታማነቱ መትጋት ወሳኝ ነው። በጉዳዩ ላይ ተከታታይ ስራ መስራት እንጂ አንዴ ሞክሬዋለሁና ሊሳካልኝ አልቻለም በሚል ተስፋ መቁረጥ አይገባም። ስኬት እስከሚመጣ መውደቅና መነሳት እንደሚኖር በማመን ለለውጡ መትጋት የሁሉም ኃላፊነት ጭምር ነው ብዬ አስባለሁ። መውደቅ እንዳለ ሁሉ መነሳት መኖሩን ተስፋ በማድረግ ወደፊት መሔድ ያስፈልጋል።

የኑሮ ወድነቱን ለማረጋጋትም ደግሞ እሱም ልክ እንደ ሰላም ማስፈን ሁሉ ትልቅ ስራ የሚጠይቅ ነው። በእርግጥ ችግሮቻችን ተደማምረው የበዙ ሆነዋል። አንዱን መፍትሔ ሊገኝለት ነው ሲባል ሌላው ችግራችን ይቀጥላልና መፍትሔው እርስ በእርስ መተሳሰብ ነው። በተቻለ መጠን የወጡ ሕጎችን ማክበር እና በእነሱ መገዛት ወሳኝ ነው። ጎን ለጎን ደግሞ መንግስትም ሕዝብም መወጣት የሚጠበቅበትን ሚና መወጣት ይኖርበታል። እንደ አጠቃላይ ሰላም መስፈን ቢችልና የኑሮ ውድነቱ ቢረጋጋ አገራችን በተሻለ ጎዳና ላይ መሆን ትችላለች እችላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ስቃስ ምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**አስምሰገድ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ።



# የራስን ምርት የመጠቀም ባህል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከዜጎች ዘንድ የሀገር ውስጥ ምርትን የመጠቀምና የማበረታታት ባህል አለመዳበርና የሀገር ውስጥ ምርትን የመናቅ ዝንባሌ ለሀገር ውስጥ ምርት አለመስፋፋት ዋነኛ መሰናክል መሆናቸው ላይ ብዙዎች ይስማማሉ።

ለመሆኑ የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም ለሀገር ምጣኔ ሀብታዊ እድገት ምን ፋይዳ ይኖረዋል? በማኅበረሰብ ዘንድ ያለው የሀገር ውስጥ ምርትን የመናቅ ዝንባሌንስ በምን መልኩ መቀየር ይቻላል? በሚሉ ጉዳዮች ላይ ያነጋገርናቸው የምጣኔ ሀብት ምሁራን የሚከተለውን ሃሳብ አካፍለውናል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት ምሁሩ አጥላው አለሙ (ዶ/ር)፣ የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም የሀገር ውስጥ ምርቶች በቁጥርና በጥራት እየጨመሩ እንዲሄዱ፣ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ፣ በሀገር ውስጥ ያሉ ጥሬ እቃ አቅራቢዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑና በአምራች ኢንዱስትሪው ውስጥ የሚሰማራውን የሰው ኃይል ለማሳደግ እንደሚረዳ ያብራራሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፣ የሀገር ውስጥ ምርትን ንቀን የውጭ ሀገር ምርቶችን ስንገዛ ግን፣ የሀገር ኢኮኖሚና አምራቾችን እየጎዳን፣ የውጭ ሀገራት ዜጎችንና ፋብሪካዎቻቸውን የምናግዝ እንሆናለን።

በዜጎች መካከል የሀገር ውስጥ ምርትን የመጠቀም ባህል ባለመዳበሩ፣ የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪዎችና እና የኢትዮጵያ ግብርና ተበድሏል ያሉት አጥላው (ዶ/ር)፣ በማኅበረሰብ ዘንድ የሀገር ምርትን የመጠቀም ባህል እምብዛም መሆኑ፣ ሀገራችን የሀገር ምርትን በመጠቀም ልታገኝ የሚገባትን ኢኮኖሚያው ጠቀሜታ ማግኘት እንዳላስቻላት ይናገራሉ።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ምርቶችን ከውጭ ለማስገባት በዓመት በአማካይ እስከ 20 ቢሊዮን ብር ስታወጣ፣ ወደ ውጭ የምትልከው ግን አራት ቢሊዮን ገደማ ብቻ መሆኑን ያነሱት የምጣኔ ሀብት ምሁሩ፣ የውጭ ምርቶችን መጠቀም ትልቅ የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቅ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

እርሳቸው እንደገለጹት፤ የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ሊሟላ የሚችል አይደለም። ይህን ችግር ለመቅረፍ ደግሞ የሀገር ውስጥ ምርትን የግድ ማበረታታት ያሻል። ምርቶቻችን የጥራት ችግር ቢኖርባቸው እንኳ በመደገፍና በማበረታታት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በምርት መጠንና ጥራት እያደገ እንዲሄድ ማድረግ ይገባል።

የሀገር ውስጥ ምርትን ለማበረታታትና የሀገር ውስጥ ምርት ተጠቃሚነትን ለመጨመር ከጥሬ እቃዎች ይልቅ ያለቀላቸው ምርቶች ወደ ውጭ የሚላኩበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባም አንስተዋል። ቀደም ሲል በምርቶቻቸው ተመራጭ የነበሩ እንደ ቆርቆሮ አምራችና መኪና መገጣጠሚያ ያሉ የሀገር ውስጥ አምራቾች የበለጠ እንዲበረታቱና በስፋት እንዲቀጥሉ አልተደረጉም ያሉት አጥላው (ዶ/ር)፣ ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ የደረሱ አምራች ኢንዱስትሪዎች ወደኋላ እንዳይመለሱና የበለጠ እየሰፉ፣ ምርቶቻቸውም እያደገ እንዲሄድ ማድረግ እንደሚገባም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ምሁሩ፣ በዜጎች መካከል የሀገር ውስጥ ምርት ተጠቃሚነትን የመጠቀም ባህል ለማዳበር የሚደረገው የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ከመሪዎች ይጀምራል ይላሉ። እንደ እርሳቸው ገለጻ፣ የሀገር ውስጥ ምርትን እንጠቀም ለማለት በቅድሚያ መሪዎች ምሳሌ ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል። የመንግሥት ተቋማትም የሀገር ውስጥ ምርትን በመግዛት አምራቾችን በተግባር ማበረታታት ለዜጎችም ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል ብለዋል። እስካሁንም ይህ ልምድ ዳብሮ ቢሆን ኖሮ የሀገር ውስጥ ምርታችን ትልቅ ደረጃ ደርሶ ነበር በማለትም ቁጭታቸውን ይገልጻሉ።

ሌላው የምጣኔ ሀብት ምሁር ወገኔ ማርቆስ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ የሀገር ውስጥ ምርትን ለማሳደግ የሀገር ውስጥ ምርት ተጠቃሚነት ማደግ ወሳኝ መሆኑ ላይ አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ። ዜጎች የሀገራቸውን ምርቶች የመጠቀም ፍላጎታቸው እየጨመረ ሲሄድ የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም እያደገ ይሄዳል ያሉት ወገኔ (ዶ/ር)፤ ይህም የሀገር ውስጥ ዓመታዊ የምርት መጠንንን በመጨመር ለምጣኔ ሀብታዊ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል ይላሉ።

እንደ ወገኔ (ዶ/ር) ሃሳብ፣ አንዳንድ ምርቶቻችን ካደጉ ሀገራት ምርቶች ጋር ሲነጻጸሩ ያነሰ ጥራት ቢኖራቸው እንኳ፣ እንደ ሀገር በማሰብ የኢንዱስትሪዎቻችንን ጅምርና ጥረት ማበረታታትና ወደ ፊት የተሻለና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ምርት አምራች የሚሆኑበትን እድል መስጠት ከዜጎች ዘንድ ይጠበቃል።

የሀገር ውስጥ ምርትን በመጠቀም የሚገኘው ጠቀሜታ እንደ ሀገር፤ እያንዳንዱ ዜጋ ላይ ዓመታዊ ገቢን በመጨመር ረገድ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው የተናገሩት ዶ/ሩ፣ ዜጎች የሀገር ውስጥ ምርትን መጠቀም እንደ ሀገር ሊኖረው በሚችለው ፋይዳ ላይ በቂ ገንዛቤ እንዲኖራቸው ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚያሻ ይመክራሉ።

# "የቱሪዝም ሳተሳይት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በሀገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የዳግም የሆቴሎች የጥራት የኮከብ ደረጃ ምደባ የተከናወነ ሲሆን፤ ውጤታቸው በቅርብ ይፋ እንደሚደረግም አመላክተዋል።

የቱሪዝም ዘርፉን ለማሳደግ የተለያዩ የሕግ ማሻሻያዎችን የማድረግ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ የመተግበር፣ የከተሞችን የቱሪዝም ብራንድ የማዘጋጀት፣ በዘርፉ የግሉን ሴክተርና የውጭ ባለሀብቶችን ኢንቨስት እንዲያደርጉ የማበረታታት ሥራ መሠራቱን አስታውቀዋል።

የቱሪዝም ሥራ መዳረሻን ማስፋፋትና ሀገርን ማስተዋወቅ ዋናው ጉዳይ ነው የሚሉት አቶ ስለሺ፤ ከዚህ ጎን ለጎንም የቱሪስቶችን ፍላጎት በማሟላት የቆይታ ጊዜያቸውን ለማራዘም እና ወደ ኢትዮጵያ ለመሳብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ባለፉት የለውጥ ዓመታት በ"ገበታ ለሸገር"፣ በ"ገበታ ለሀገር" እና በ"ገበታ ለትውልድ" በተሰኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎችን ማልማት መቻሉን ገልጸው፤ በዚህም በሀገሪቱ በፊት ከነበሩት እጥፍ የሚሆኑ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ለምተዋል ብለዋል።

የፕሮጀክቶቹ መገንባት የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን ቁጥር ለመጨመርና የቆይታ ጊዜያቸውን ለማራዘም፣ የውጭ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግ፣ ለሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ማህበራዊ መስተጋብርን ለማጠናከር፣ የሀገሪቱን ገጽታ ለመገንባትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻ ቦታ ባለቤት እንድትሆን ማስቻሉን አብራርተዋል።

የቱሪስት መዳረሻዎች ከማስተዋወቅ አንጻር በሀገር ውስጥ እና ከዚህ በፊት ተቋርጦ በነበረው በጀርመን፣ በእንግሊዝ እና በተለያዩ የዓለም ሀገራት በቱሪዝም ሚኒስቴር እና በግሉ ዘርፍ በኩል የማስተዋወቅ ሥራ መሠራቱን አንስተዋል።

የሀገሪቱን የቱሪስት ቦታዎች በሀገር ውስጥ ሚዲያዎች ከማስተዋወቅ ባለፈም የብራዚል፣ የሩሲያ፣ የቻይና እና የሌሎች ሀገራት ሚዲያዎች እንዲጎበኙና እንዲያስተዋውቁ የማድረግ እንዲሁም የቢዝነስ ለቢዝነስ ትስስሮች፣ ኤግዚቢሽኖችን እና ሌሎች የማስተዋወቂያ ፕሮግራሞች መከናወናቸውን ጨምረው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ከምትታወቅባቸው በተጨማሪ በርካታ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች ስላሏት አውሮፓና ሰሜን አሜሪካ ብቻ ተንጠልጥሎ የነበረውን የቱሪዝም ገበያ ወደ አፍሪካ ለማምጣት በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

# ለውጣ ውረድ ያልተበገረው የህዳሴ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በአቅማቸው ልክ አዋጥተዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ህዳሴን ሲሠሩ በሌላ በኩል ደግሞ ጊዜን፣ ሀብትንና ገንዘባቸውን አውጥተው ዓለም አቀፍ ጫና ለመፍጠርና በሀገር ውስጥ የተለያዩ ኃይሎችን በማስታጠቅ የሚሠሩ አሉ። በአንድ ሀገር ውስጥ አንዱ ለልማት ሌላኛው ለጥፋት ይሠራሉ። በዚህ አስቸጋሪ ሂደት ውስጥ ግድቡ አስደናቂ በሆነ መንገድ ውሃ ይዟል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አብራርተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳብራሩት፤ ለማደግና ለመለወጥ ወደ ሥራ ስንገባ ዓለም ሁሉ አጨብጭቦ የሚቀበለን ባለመሆኑ ከወትሮው መንገድ በተለየ መደማመጥና ለጋራ ዓላማ መቆም አስፈላጊ ነው። ባለን ጉልበትና ገንዘብ መተባበር አስፈላጊ ነው፤ ካልሆነ ስንዴው፣ የአረንጓዴ ዐሻራው፣ የኮሪደል ልማቱና የህዳሴው ግንባታ በዋዛ ፈዛዛ ሊሳካ አይችልም ነው ያሉት።

ለህዳሴ ግድብ የከፈልነው ዋጋ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ስትራቴጅክ እሳቤውን ተገንዝቦ ቢሆን ብዙ ዋጋ ባልከፈልን ነበር። ከዚህ መማር ያስፈልጋል። ሱዳንና ግብጽ መደገፍ ያለባቸው ግድብ ነው፤ በቀን እስከ ዘጠኝ መቶ ሚሊዮን ሜትር ኪዩቢ ውሃ ይይዛል። አጠቃላይ የመያዝ አቅሙ 74 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢ በመሆኑ በ74 ቀን ውስጥ ሙሉ ውሃውን መያዝ እንችላለን። ሌላው ቢቀር በ100 ቀን ውስጥ ግድቡ ሙሉ ማድረግ እንደሚቻል ያብራራሉ።

ይህ ደግሞ ታችኛው ተፋሰስ ሀገራት በማንኛውም ጊዜ ተጨማሪ ውሃ ቢስፈልጋቸው በቀላሉ መጠቀም ይችላሉ፤ ይህ የሚሆነው ግን ውሃውን መያዝ ሲቻል መሆኑን ገልጸዋል። አሁን ላይ አራት ተርባይኖች ኃይል እያመረቱ ነው። በቀጣይ አራት ወራት ውስጥ ተጨማሪ ሶስት ተርባይኖች ሥራ ይጀምራሉ። ታህሳስ ላይ ሰባት ተርባይኞች ኃይል ያመርታል። አጠቃላይ ሥራው ከአንድ ዓመት በኋላ ይጠናቀቃል ሲሉም ገልጸዋል።

ህዳሴን ከሞላ ጎደል ጨርሰነዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ከዚህ በኋላ በህዳሴ ጉዳትና ስጋት የለንም፤ ለማደናቀፍ የሞከሩ ኃይሎች ጉዳት አድርሰው ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን አላቆሙንም። ሥራውን ጨርሰነዋል። ያወጡት ገንዘብ፣ ጉልበትና ድካም ከንቱ ሆኖ ቀርቷል። ነገር ግን ህዳሴን ለመደገፍ ቢያውሉት በተሻለ ትብብር ጥቅም ላይ ሊውል ይችል ነበር። በርካታ ኢትዮጵያውያን ከህዳሴ ግድብ ግንባታ ለአፍሪካ የሚተርፍ ልምድና እውቀት ማግኘታቸውን ነው የተናገሩት።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስርት አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ከሰሞኑን በአፍሪካ ቀንድ ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ የህዳሴን ግድብ በተመለከተ ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ዝግጁ ናት። ብዙ የሚያለያየን ጉዳይ የለም፤ ችግር የሆነው በግብጽ በኩል ፖለቲካ እየተቀላቀለበት ነው። የናይል ስምምነት ማዕቀፍ በተፋሰሱ ሀገራት እየተፈረመ ነው። የፈረሙ ሀገራም ሰነዱን ለአፍሪካ ህብረት እያስገቡ ነው፤ ያልፈረሙም ፈርመው በአንድ ማዕቀፍ ውስጥ እንሥራ የሚል ፍላጎት ኢትዮጵያ እንዳላት አብራርተዋል።

የናይል ስምምነት ማዕቀፍ ከላኛው የተፋሰሱ ሀገራት ይልቅ ለታችኞች የተፋሰስ ሀገራት በጣም ጠቃሚ ነው። ህዳሴ በርካታ ፈተናዎችን አልፎ ወደ መጠናቀቁ መድረሱን አንስተዋል።

የህዳሴው ግድብ ተሚጋችና የኪንግስ አፍ ዓባይ ሚዲያ ምክትል ኃላፊ ዛሂድ ዘይዳን በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የህዳሴ ግብድ በ2020 ብዙ ውሃ አልያዘም ነበር። ነገር ግን የሥራ እንቅስቃሴው አስደሳች ነበር። ስለ ህዳሴው ብዙ አሉታዊ ነገሮች በሚወሩበት ጊዜ የነበረው የሥራ እንቅስቃሴ አስደሳች ነው።

በአሁኑ ጊዜ ህዳሴ ግድቡ የሚገኝበት አካባቢ አየር ንብረቱ ሙሉ ለሙሉ ተቀይሯል፤ ከፍተኛ ሙቀት ነበር፤ አሁን ላይ ሙሉ ለሙሉ አረንጓዴ ስለመሆኑ ገልጸዋል። አሁን ላይ ህዳሴ በርካታ ችግሮችን አልፎ 62 ቢሊዮን ሜትር ኩዩቢ ውሃ መያዙ ትልቅ ስኬት ነው። ለህዳሴው ግድብ የለፉ ሁሉ የሚደሰቱበትና ልፋታቸው ፍሬ እያፈራ ስለመሆኑ የሚያስገነዘብ ነው ይላሉ።

አሁን የታየው የህዳሴ ግድብ ስኬት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ርብርብ ነው ያሉት ምክትል ኃላፊው፤ 62 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢ ማለት ትርጉሙ ብዙ ነው። ግድቡ ቆሟል፣ ለግብጽ ተሸጧልና መሰል አውንታዊ ለሆኑ መረጃዎች ምላሽ የሰጠ ነው። የፖለቲካ ተቋውሞ ያላቸው ዜጎች ግድቡንና ፖለቲካን መለየት አለባቸው ነው ያሉት።

አሁን ብዙ ለውጥ አለ፤ ለማለቅ ወደ ጫፍ ደርሷል። አሁን ላይ የውሃ ፍሰት እንደሚያሳየው የግድቡ ርዝመት 628 ሜትር መድረሱን ነው። ይህ ማለት ደግሞ ግንባታው ወደ መጠናቀቁ እየደረሰ ነው። እንዲሁም ከ60 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢ በላይ ውሃ እንዲይዘ ያስችለዋል። ግድቡ 74 ነጥብ 2 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢ ውሃ ይይዛል፤ አሁን ላይ ከ98 በመቶ በላይ ውሃ ይዘናል። ይህ ደግሞ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ህልም እውን ስለመሆኑ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ዛሂድ ገለጻ፤ ግድቡ ከተጀመረበት ጊዘ ጀምሮ የነበሩ ዛቻዎችንና ዓለም አቀፍ ጫናዎችን ተቋቁሞ 62 ነጥብ 1 ቢሊዮን ሜትር ኪዩቢ ውሃ መያዝ መቻሉ የኢትዮጵያን ጽናት ያሳያል። ግድቡ ውሃ እንዳልያዘ ተደርጎ ሲነዙ የነበሩ የተሳሳቱ መረጃዎችን በገሀድ ያጋለጠ ነው። ያመጣው የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ በመሆኑ ጠቀሜታው ለሁሉም ነው። ኃይል የሚያመነጩ ተርባይኖችም እየበዙ ነው፤ ይህ ደግሞ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ትልቅ ኩራት ነው ሲሉ 2016 ዓ.ም ስኬትን ነው ያብራሩት።

በአዲሱ ዓመትንም ሌላ ስኬት የሚመዘገብበት፣ ኢትዮጵያ ሁለተናዊ ዕድገት የሚረጋገጥበት እንደሚሆን ተስፋቸውን ገልጸዋል።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የአምራች ዘርፉን እድገት የሚያፋጥኑት የኢንዱስትሪ ፓርኮች

አንተነህ ቸሬ

የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሰረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ስራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብሰብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሰረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያም ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፈልባቸውን የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖች ከቀረጥ ነፃ ማስገባትን፣ የብድር አቅርቦትን፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን እና የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል።

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ (Manufacturing Hub) እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤቶች ተገኝተውበታል። በተለይም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድሎችን በመፍጠር ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ አበርክተዋል።

በአሁኑ ወቅት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ።

የእነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሳደግ ከተደረጉት ጥረቶች መካከል የሚጠቀስ ሲሆን፣ በመንግሥት እየተወሰዱ ያሉትን የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ፓርኮቹም ዘርፉን የማሳደግ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ፍስሃ ይታገሱ፣ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት መንግሥት የአምራች ዘርፉን በተቀናጀ መልኩ ለመደገፍና ለማልማት ከወሰዳቸው ተግባራዊ እርምጃዎች መካከል አንዱ እንደሆነ ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ የግል እና የተቀናጁ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ሳይጨምር ለሌሎቹ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመገንባት ብቻ መንግሥት ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጭ አድርጓል። ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ መንግሥት የአንድ መስኮት አገልግሎትን ጨምሮ የተቀናጀ መሰረተ ልማት ያቀረበባቸው የማምረቻ ቦታዎች ናቸው። 85 በመቶ የሚሆኑት የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ሼዶች በባለሃብቶች ተይዘዋል።

ፓርኮቹ ሲሰሩ ታሳቢ ተደርጎ የነበረው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች እንዲመረቱባቸው ነበር፤ በዚህም አብዛኞቹ ፈቃድ የወሰዱት የውጭ ባለሃብቶች ነበሩ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች በተሰጠው ትኩረት አማካኝነት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መጥቷል። በአሁኑ ወቅት በፓርኮቹ ውስጥ ከሚገኙት ኢንቨስተሮች መካከል ከ51 በመቶ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ አምራቾች እስካሁን ለውጭ ገበያ ካቀረቧቸው ምርቶች ከአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል። ከወጪ ንግድ በተጨማሪ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትኩረት በተሰጠው የተኪ ምርት ዘርፍም ተስፋ ሰጭ ውጤቶች እየተመዘገቡበት ይገኛል። በዚህም እስካሁን ከ750 ሚሊዮን ዶላር በላይ ዋጋ ያላቸው ተኪ ምርቶች ተመርተዋል። በስራ እድል ፈጠራ ረገድ ከ70ሺ በላይ ሰራተኞች በኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ውስጥ ተቀጥረው እየሰሩ ይገኛሉ።

የወጪ ንግድ (Export Trade) አፈፃፀም ዝቅተኛ እንዲሁም በአምራቾችና በግብዓት አቅራቢዎች መካከል ያለው ትስስር (Linkage) ደካማ መሆኑ፣ ውስጣዊና ዓለም አቀፍ አለመረጋጋቶች፣ ጥሬ እቃን በሀገር ውስጥ ምርት ያለመተካት ድክመት፣ የስራ እድል ፈጠራው በቂ አለመሆን፣ የውጭ ምንዛሪ እጥረት፣ የቢሮክራሲ ውስብስብነት እንዲሁም የመሰረተ ልማት ጥገና ክፍተቶች በመንግሥትና በባለሃብቶች በኩል ያሉ የዘርፉ ልማት ተግዳሮቶች እንደሆኑም ዋና ስራ አስፈፃሚው ይገልፃሉ።

ሀገራት የኢንቨስትመንት ዘርፋቸውን በማሳደግ ጥቅል አገራዊ እድገታቸውን ዘላቂ ለማድረግ ከሚተገብሯቸው አሰራሮች መካከል አንዱ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን (Special Economic Zones) ማቋቋም ነው። ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የሚፈጥሩትን የስራ እድል፤ ለአገር በቀል የሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪው መስፋፋት የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰትን፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርንና የባለሙያዎችንና የሠራተኞችን ክህሎት ለማሳደግ እና የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ የሚኖራቸውን ወሳኝ ሚና እንዲሁም የወጪና ገቢ ንግድን ለማቀላጠፍ ያላቸውን አበርክቶ በአጠቃላይ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት መሻሻል የሚኖራቸውን ጉልህ ፋይዳ ከግምት ውስጥ በማስገባት አገራት ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን ያቋቁማሉ፣ ያስፋፋሉ።

በኢትዮጵያ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን በማቋቋም የሀገሪቱን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተለያዩ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ። ግንባታቸው እየተከናወኑ ከሚገኙት ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች የማሸጋገር ጥረት ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎችን የማስፋፋት እንቅስቃሴ አካል እንደሚሆን ሲገለፅ ቆይቷል። ከሁለት ዓመታት በፊት ከኢንዱስትሪ ፓርክነት ወደ ነፃ የንግድ ቀጣናነት ተሸጋግሮ ስራ የጀመረው ድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናም የዚሁ ማሳያ ነው።

በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ኢንዱስትሪ ፓርኮቹን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለማሸጋገር እንደታቀደ ዶክተር ፍስሃ ይናገራሉ። በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና የተጀመረውን ስራና ልምድ

> **በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና የተጀመረውን ስራና ልምድ ወደሌሎች ኢንዱስትሪ ፓርኮች በማስፋት፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለማሸጋገር ታቅዷል። በነፃ የኢኮኖሚ ቀጣናዎቹ ከምርት ስራዎች በተጨማሪ የንግድና የሎጂስቲክስ ተግባራትም ይከናወናሉ**

ወደሌሎች ኢንዱስትሪ ፓርኮች በማስፋት፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹን ወደ ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣናዎች ለማሸጋገር ታቅዷል። በነፃ የኢኮኖሚ ቀጣናዎቹ ከምርት ስራዎች በተጨማሪ የንግድና የሎጂስቲክስ ተግባራትም ይከናወናሉ።

ከዚህ በተጨማሪም ፓርኮቹ በብዙ ዘርፎች የሚሰማሩ ባለሃብቶችን እንዲቀበሉ ማድረግ እንደሚስፈልግ ጠቁመው፣ በአንድ የምርት ዘርፍ ላይ ብቻ ያተኮሩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች በሌሎች ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶችን እንዲያስተናግዱ እንደሚደረግና ለተኪ ምርት የተሰጠው ትኩረትም ይበልጥ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ዋና ስራ አስፈፃሚው ያብራራሉ።

መንግሥት ባለፉት ጥቂት ዓመታት የወሰዳቸው የምጣኔ ሃብት ማሻሻያ እርምጃዎች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የተሰማሩ ባለሃብቶችን ተጠቃሚ እንደሚያደርጉ የሚያስረዱት ዶክተር ፍስሃ፣ ማሻሻያዎቹን በብቃት በመተግበር ተጨማሪ ኢንቨስትመንትን መሳብ እንደሚገባ ይገልፃሉ።

«በቅርቡ መተግበር የጀመረው በገበያ ላይ የተመሰረተ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር ስርዓት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለተሰማሩ/ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ዘርፍ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። የውጭ ባለሃብቶች በጅምላና ችርቻሮ ንግድ እንዲሰማሩ መፈቀዱም የውጭ ባለሃብቶችን ወደ ሀገር ውስጥ ለመሳብ ተጨማሪ እድል ይፈጥራል። የካፒታል ገበያ እንዲጀመር የሚደረጉ ዝግቶች ከዚህ ቀደም በባንኮች ላይ ተንጠልጥሎ የነበረውን ካፒታል ለማግኘት ያስችላል» ይላሉ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል በበኩላቸው፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በርካታ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን በማድረግ የአምራች ዘርፉን ብሎም ሀገራዊ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ጥረት ስለመደረጉ ይገልፃሉ።

እሳቸው እንደሚናገሩት፣ ባለፉት ስድስት ዓመታት የአምራች ዘርፉን አፈፃፀም በማሻሻል በሀገር ውስጥና በውጭ ተወዳዳሪ ለመሆን በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተደርገዋል፤ ቅንጅታዊ አሰራሮችና የባለድርሻ አካላት ትብብሮች እንዲጠናከሩ፣ የኃይል አቅርቦት እንዲሻሻል፣ የሎጂስቲክስ ስርዓቱ እንዲዘምን እና ለአምራች ዘርፍ የሚቀርበው የፋይናንስ መጠን እንዲጨምር ተደርጓል። የዘርፉን ውጤታማነት ለማሳደግ የተከናወኑት ተግባራት ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ የአምራች ዘርፍ ተግዳሮቶችን ለማቃለል አስተዋፅዖ ነበራቸው፤ የዘርፉ ዓመታዊ እድገት 10 ነጥብ አንድ በመቶ እንዲሆን አስችለዋል።

አቶ መላኩ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርቶች እሴት ተጨምሮባቸው ለገበያ እንዲቀርቡ ትልቅ ሚና እንዳላቸው ያስረዳሉ። «በ2016 የበጀት ዓመት ወደ ውጭ ከተላከው ምርት ውስጥ 78 በመቶ የሚሆነው በጥሬ የተላከ ነው። በምርቶች ላይ እሴት ጨምሮ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይገባል። ይህን ለማድረግ ደግሞ በአምራች ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሃብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መግባት እና ኢንዱስትሪ ፓርኮችም በሙሉ አቅማቸው ማምረት ይጠበቅባቸዋል። የምጣኔ ሃብት ማሻሻያዎችን የሚጠቀም ባለሀብት ያስፈልጋል። ባለሀብት ገብቶ ካልሰራበት ፖሊሲውም ሆነ መሰረተ ልማቱ ብቻውን ለውጥ አያመጣም» ይላሉ።

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና እድሎች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት ሀገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም። ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል።

የአምራች ዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው። ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል። ይህም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የመሰረተ ልማት ግብዓቶች፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል።

# ከርታታው ገብርዬ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ገብርዬ እልም ካለ የሕልም አጀብ ውስጥ ሰምጦ ሲቃዥ ሲወራጭ ነበር። ብንን! ብሎ እንደነቃ ሕልምና እውኑ ተጋጭቶበት የትኛው በእውን፣ የትኛው ደግሞ ሕልም እንደነበረ ግራ እንደገባው ለአፍታ ብዥ አለበት። በላብ ከተጠመቀው ሰውነቱ ጋር ከእንጨት አልጋው እንደተቀመጠ ከውጭ የሚሰማው የሆታ ድምጽ የእውን መሆኑ አወቀና ይባስ ግራ ገባው።

**“ሆ! ብስን መጣን ሆ! ብስን**
**አባባ አሱ ብስን…”**

ትዝ ሲለው “ለካስ ዛሬ አውዳመት ነው” አለ በለሆሳስ። ሁሉንም ነገሩን ካጣ ወዲህ ዓመት በዓልን አያውቃትም። ምንም ነገር ኖሮት ምንም አያደርግም። የፊቱ ፈገግታ ርቆ የዓይኑ እንባ ከደረቀ ሰነባብቷል። በመሃል ያ የልጃገረዶች “አበባየሆሽ” ድምጽ ተቋርጦ ሌላ የግርግርና የሩጭ ደፍ! ደፍ! ከእግሮች የትርምስ ኮቴ ጋር ከጆሮው ገባ። ቤቱ ያለችው ከመስቀለኛ መንገድ ዳር ላይ ከመሆኗም አጥር የላትም። አራቱንም መንገድ ከአንድ የሚያገናኘው ስፍራ የመንደሩ ልጆች የኳስ መጫወቻ ሜዳ ናት። መንገደኛው ሁሉ ቤቱን ታክኮ ያልፋል። ዛሬ ደግሞ ለመንቃት በማይፈልግበት ዕለት በጠዋቱ ቀሰቀሱት። “ናአርዲናት!” ብሎ ተመልሶ ጋደም አለ። እንቅልፍ አልመጣ ቢለው ሲያይ የቆየውን ቅዠት እያሰላሰለ አንዳች ፍርሃት ተሰማው። ምን ሆኜ ነው? ለምንድነው እንዲህ የሆንኩት? ማነው እንዲህ ያደረገኝ? እያለ ምላሹን ሊቆፍር ሲል የጠፋው ትርምስ መልኩ ቀየሩ መጣ። ከውጭ የልጆች ጩኸትና ግርግር ሰማ። ግርግዳው በቡጢ ይሁን በእርግጫ ድው! አድርጎ ያለፈ አንድ ጎርነን ያለ የልጅ ድምጽ “አንተ መላጣ! የመላጣ…ደረትህን ነፍተህ ሰፈራችን ድረስ ትመጣለህ! ምንም አያመጡም ብለህ ንቀት ነዋ! ዳዋ በናተ አንዴ በደንብ አስገባለት…” ሌላ ቀጭን ድምጽ እሪ ይላል! “ዝም በል አንተ ሴታሴት! ሳልጨምርልህ አፍህን ዝጋ!” እንደገና ስቅ! ስቅ! እያለ ሄዶ ድምጹ ታፈነ። ገብርዬ ዘሎ ከአልጋው በመውረድ በሩን ከፍቶ ወጣ። ደጁ በነጭ የወረቀት ብጭቅጫቂ ተሞልቶ በሂልኮፕተር የተበተነ ይመስላል። ዞር ብሎ ከአንደኛው የጎዳና ጥግ ሲመለከት ገሚሱ ዱላ፣ ገሚሱ የውሀ ሲፎን ቁርጥራጭ የያዙ የመንደሩ ልጆች ሰብሰብ ብለዋል። “ይሄ የማፍያ ጥርቅም ሁላ በሌሊት እንቅልፍ ይነሱኝ!” እያለ ጠጋ አለ። ገብርዬን እንደተመለከቱ አንዳንዶቹ ፈትለክ ብለው ሮጡ። የተመለከተውን ነገር ለማመን አቃተው።

ዙሪያውን ከበው ሲነርቱትና ሲጫወቱበት የነበረ አንድ ልጅ ከመቦጫጨቅ ያስመለጣቸውን ሁለት የአበባ ስዕሎች ጭምቅ አድርጎ እንደያዘ ፊቱን በወረቀቱ ከልሎ ከእግራቸው ስር ቁጢጥ ብሏል። አዲስ የሚመስለው ልብሱ በጭቃ ተለውሷል። “ምንድነው ጉዱ! እኮ ምን እያደረጋችሁልኝ ነው? …ምድረ ባፉንኩሉ! ተናገሩ እናንተን እኮ ነው!” አንባረቀባቸው። ማንም ምላሽ የሰጠው አልነበረም። ግማሹ ደረቱን እንደነፋ ሌላው አቀርቅሯል። ገብርዬ መሀከላቸው በምርኮ የተደፋውን ልጅ አስነስቶ በእጁ ከያዘው በኋላ ረጋ ብሎ “ጆንትራው! በል እስቲ አንተ ንገረኝ። ልጁን ምን እያደረጋችሁት ነበር?” ጸጉሩን ጆንትራ ተቆርጦና ያለ ዕድሜው ሰውነቱ ተኮፍሶ የልጅ ወጠምሻ የመሰለው የ13 ዓመት ልጅ “አምና ቹቹና ዳግም ስዕል ሊሸጡ ወደ እነርሱ ሰፈር ሲሄዱ የነርሱ ሰፈር ልጆች ተሰባስበው መቷቸው። ስዕል የሸጡበትንም ብራቸውን ወስደውባቸዋል። እናም በቃ እኛም ዘንድሮ የነርሱ ሰፈር ልጆች ስዕል ለመሸጥና ሴቶቹም ለአበባየሆሽ ሲመጡ እንበቀላቸዋለን ብለን ተነጋገርንና ጠዋት ተደብቀን ጠበቅናቸው። ሴቶቹ ሊጨፍሩ ሲሉ አባረርናቸው። እርሱንም ጠብቀን ያዝነው…” የሰማውን ነገር ለማመን ከበደው። ጆሮውን ተጠራጠረ። “እናንተ ምንም በሌለው ነጭ ወረቀት ላይ የተሳላችሁ ነበራችሁ። እናንተ አይላችሁም እኛ ነን የቀደድናችሁ! እኛ ነን እዚህ መስቀለኛ መንገድ ላይ የጣልናችሁ። ገና የፍቅርን ጡት ጠብታችሁ ሳትጨርሱ ማነው ይህን የበቀል እርግማን ያወረሳችሁ!…” እያለ ጮኸ። ከእጁ የሚነፋረቀውን ልጅ ካባበለው በኋላ “ዳግም እና ቹቹ እስቲ ኑ!…ከናንተ መካከል ይሄ ልጅ የመታው ማንን ነው?” ማንንም በሚል አቀርቅረው ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ። “እሺ ሁላችሁም መልሱልኝ…ማናችሁን ነው የበደለው?” አሁንም ሁሉም ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ። “እና የርሱ ጥፋት የዚያ ሰፈር ልጅ መሆኑ ነው ማለት ነው…እስቲ አሁንም መልሱልኝ፤ የዚህ ሰፈር ልጅ ለመሆን መርጦ የተወለደ ከመካከላችሁ ማን ነው?” ዝምታው ሲበዛ በዙር እያንዳንዱን ጠየቃቸው። ሁሉም የሰጡት ምላሽ ማንም የሚል ነበር። ገብርዬ ግን ውስጡን እንደ እሳት እየለበለበው ቀጠለ። “በሰፈሩ ውስጥ አድፍጦ የሚናከሰውና በበቀል የሚባላው ውሻ ብቻ ነው። እናንተ ደግሞ የሰው ልጆች፣ ያውም ኩሩ ሐበሻ! ኩሩ ኢትዮጵያዊ ናችሁ። ሀገራችሁ ከናንተ የምትጠብቀው ይህንን ዱላና ጎማ አይደለም። በሉ አሁን ሁላችሁም የያዛችሁትን ጣሉ!” ሁሉም የያዘውን ወረወረ። ገብርዬ የልጆቹን የጸጸት ፊት እየተመለከተ በቁም ነገር የሁለቱንም ሰፈር ልጆች ለማስታረቅ ለሌላ ቀን ቋጠሮ ያዘላቸው። ለቀደዱበት ስዕል አውጥቶ ኪሱ የነበረውን ሰጠው። ልጁ ጥቂት እርምጃዎችን እንደሄደ “ጆሴ!” ሲል ቅድም የኮረኮመው ልጅ ጠራው። ገብርዬም ከቤቱ በር ላይ ደርሶ ወደኋላ ዞሮ ተመለከተ። ልጆቹ ኪሳቸው የነበረውን ጥቂት ብር ሰብስበው ሲሰጡት ተመለከተና ከልቡ ደስ አለው። ፈገግ እያለ ዘልቆ ወደ ውስጥ ገባ። እንዲህ ደስ ብሎት አያውቅም ነበር።

***

ወደ ቤት እንደገባ ጠኔ አንቆ ሊደፋው ደረሰ። “አዕምሮ እጅግ የዋህ ነው በቀላሉ ሊያታልሉት ይችላሉ። ሆድ ግን ደልለው የማያመልጡትና ምህረትን የማያውቅ የሰይጣን ቁራጭ ነው!” እያለ ሲራገም ከማታ የተረፈችውን ቁራሽ አንባሻ ከጠረጴዛው ላይ አንስቶ ከነፌስታሉ ግምጥ አደረጋት። ስለራበው የሚበላ ቢመስለውም ገና የመጀመሪያዋ ጉርሻ ከአፉ አልላመጥ፣ ከጉሮሮ አልወርድ ብላው ተሰነቀረች። ከኮዳው ውሀ ፉት ብሎ እንደምንም በትግል አወረዳት። በድጋሚ አልጎረሰም። መልሶ እንዳስቀመጣት የሲጋራዋን ፓኮ አንስቶ ሁለቱን አከታትሎ አቀጣጠለ። ደጅ ወጥቶ ጸሐይዋን መሞቅ ጀመረ። እዚያው እንደተቀመጠ የምን ጊዜም ጠላቱ በርጉ በሙሉ ነጭ የበዓል ልብሱ ሽክ ብሎ ከ12 ዓመት ልጁ በናያስ ጋር ወደ ቤቱ እያለፈ ሁለቱም እኩል ተያዩ። በርጉ ያን የአሸዋ ግርፍ ከመሰለው ፊቱ ስር ያሉትን ትልልቅ ከናፍሮቹን አሳስሞ እንደሚሽሟጠጥ አድርጎት አለፈ። የገብርዬ ዓይን ግን ትንሹ በናያስ ላይ ነበሩ። አባቱን ፈርቶ እንጂ በናያስም ሲሮጥ መጥቶ ቢጠመጠምበት ደስ ባለው ነበር። በዚህም ብዙ ጊዜ ዱላና ቁጣ ወርዶበታል። ገብርዬ የበርጉ አጎትነትና ለዚህ የበቃበት የኑሮ ምስቅልቅል ሁሌም ራሱን እየጠየቀ፣ ሁሌም ምላሽ እንዳጣ ነው። የማይፈታ፣ ፍቺው ያልታወቀ እንቆቅልሽ…

“ገብርዬ!…ገብርነት!” ዞር ሲል በአካባቢው የታወቀ የበግ ነጋዴ የሆነው ቆሬ ነበር። ከማጠሩ መወጠሩ ማለት ለርሱ ነው። በዚያ ድንክዬ ቁመቱ ላይ ውፍረት፣ ከውፍረቱ ላይ ቦርጭ፣ ተደማምረው አሻንጉሊቷን ላላን አስመስለውታል። እንደተቻኮለ መጥቶ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ … ገብርዬ ሁሌም አንጀቴን ትበላዋለህና እንዲያው ስላሳዘንከኝ አላስችል ቢለኝ አንድ ነገር ልንገርህ ብዬ ነው” ከማለቱ “አሄሄ! ቆሬ ምነው ስንተዋወቅ…ባይሆን የመጣህበትን ንገረኝ” አለው። “ሳትሸጥ የቀረች አንዲት ወጠጤ በግ አለችኝና በዓሉን ጾም ከምትውሉ አንተና ጓደኛህ ጆሬ ለምን ቅርጫ አትገቧትም ብዬ ነው።” ገብርዬ የምሩን የሚመስል ረዥም የብሶት ሳቁን ለቀቀና “ቀድሞስ መች አጣሁህ… እንግዲያውስ ካዘንክልን አይቀር ብሩን ከበዓል መልስ እንፈልግልህ…” አለው። ቆሬ ከጥቁር ቦርጩ ላይ የበቀለውን ጸጉር እያፍተለተለ “ገብርዬ ሥራ ሥራ ነው። ምን ተይዞ ለናንተ ሁለታችሁም ያው…” አቋረጠውና “በቃ! ተወው” አለ ገብርዬ። ደግ መልከ መልካም፤ እማማ ይታይሽ ነበሩ ዛሬ እዚህ ለመድረሱ። እሳቸው ነበሩ በሰርክ አውዳመቱ። ግን ከሞቱ አምስት ወራት አለፉ። ያ ኢትዮጵያውነት፣ ያ መልካምነት፣ ያ ፍቅር፣ ያ የአውዳመት ደስታ ለካስ እሳቸው ነበሩ። “አንድ ሰው እልፍ ማኅበረሰብ…” ሲል ቆሬን ከሸኘ በኋላ የቆጡን የባጡን መቧጠጡን ቀጠለ።

> **ከኮዳው ውሀ ፉት ብሎ እንደምንም በትግል አወረዳት። በድጋሚ አልጎረሰም። መልሶ እንዳስቀመጣት የሲጋራዋን ፓኮ አንስቶ ሁለቱን አከታትሎ አቀጣጠለ**

ገብርዬ ከደጅ ወደ ቤት ለመግባት ስላስጠላው እንደተቀመጠ ሰዓታት አለፉ። ቅድም ስታሞቀው የነበረችው ጸሐይ አናቱን ላይ መተርኮስ ጀመረች። እጁን ወደ ኪሱ ሰዶ የዛገችውን ዲስኮ የእጅ ሰዓቱን አውጥቶ ተመለከተ። 5 ሰዓት ለመሆን የቀረው አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር። ተአምር ቢጠብቅም ተአምር አጣ። ያለውን ብር ደመረው…55 ብር ብቻ ነበር። “በዚህች መቼስ በሬ አልጥልባት ነገር…ሽሮዬን እንዳልበላ እንኳን የአሰጋሽ ሽሮ ቤትም ዛሬ ዝግ ነው…” እያለ በሩን ገርበብ አድርጎ ወጥቶ ሄደ። የትና ወዴት እንደሚሄድ ግን አያውቅም። ገብርዬ ካለው እንኳንስ ገንዘብና ለሰው ነብሱን የሚሰስት አልነበረም። ሰው ፊት ቆሞ በሰው ዓይን መገረፍን ስለማይወድ በረሀብ ቢሞት እንኳን አበድሩኝ ብሎ አይጠይቅም ነበር፤ ትናንት ግን የሞት ሞቱን እያንዳንዱ ደጅ ሲጠና ውሎ ማንም አምኖ እንካ ያለው አነበረም። ራሱን ረገመው።

ብዙ ቤቶችን አልፎ ከሄደ በኋላ “ኑ ጠጡ ጠላና ጠጅ ቤት”ን ሊያልፍ ብሎ ሳያልፈው ገባ። “በዚህች ገንዘብ ማድረግ የምችለው ነገር መጠጣት ብቻ ነው…” ሲል አሰበ። ገብቶ እንደተቀመጠም “ቆዳ! ቆዳ! የበግ የፍየል… ካለ ቆዳ!” እያለ በየመንደሩ ለበዓሉ የተሰውቱን የእንስሳት ቆዳ ገዢን ድምጽ የሰማው ገብርዬ ሙሉውን ብርሌ ጠጅ በአንድ ትንፋሽ ጅው! አድርጎ

**“ቆዳስ ሞልቶልሃል ዝለቅ ከየቤቱ**
**ስጋችንን በልተው ከዘለዘሉቱ፤**
**ነብሰ ቀማኞች ቤት እያዩ ማጀቱ፤**
**ተሰቅሎ የለም ወይ ባይነት ባይነቱ።”**

አለና ብርሌውን ከጠረጴዛው ጋር አገጫጨው። የኮረኮሩት ያህል በሳቅና በጭብጨባ የደመቀው ጠጪ ሁሉ “አንዱ በኔ ነው! ቅጂለት!” እያለ ጋባዡ በረከተ። ገብርዬ ከነጋ አንዲት አፍ ባልቀመሰው ሆዱ ጠጁን ባናት ባናቱ ያንቆረቁርበት ጀመረ። የጓደኛውን የነመራው ጀሬን መምጣት ባይኑ ሲጠባበቅ ብዙ ሰዓት ቢያልፍም ዛሬ ግን ያለወትሮው ሊመጣ አልቻለም። ከዚያው ያሉትን ሲጠይቅ ከእርሱ ቀደም ብሎ መጥቶና በዛሬ ቀን እንዴትስ ያለወንድሜ ልቀመጥ ብሎ እርሱን ፍለጋ እንደወጣ ነገሩት። ጠበቀ…ጠበቀ ግን አሁንም አልመጣም። ሰዓቱ ገፍቶ እየሮጠ ሳያስበው ሰማዩ መጥቆር ጀመረ። ጭለማው ከምድር ላይ እየተንሰራፋ፣ ከላይ ሰማዩ ማጉረምረም ጀመረ። አልፎ አልፎ የሙብረቅ ብራቅ ድምጽ እየተተኮሰ ልብ ይሰነጥቃል። ምሽት ሲሆን በዚያ ጭለማ መሃል፣ በዚያ ዶፍ በረዶው ከአናቱ እየወረደ፣ ሲወድቅ ሲነሳ ወደቤቱ አመራ። ከእርምጃዎቹ የወደቀባቸው ጊዜያት ይበልጣሉ። ባያስታወስም ግንባሩ ላይ ሀይለኛ ግጭት አርፎበት ነበር። እንደምንም የቤቱን በር ገፋ አድርጎ ወደ ውስጥ ሲገባ ከእግሩ ስር ኳኳታ ተሰማው። ባያውቀውም ቀን ላይ የዚያ ጠላቱ ሚስት በክዳን ሳህን አድርጋና ከባሏ ደብቃ በልጇ በናያስ የላከችለት የበዓል ምግብና መጠጥ ነበር። ግን መልካምነቷ ረፈደ። አላወቀውም እንጂ ገብርዬ ጭንቅላቱ እየደማ ነበር። ገብቶ ከአልጋው ላይ ተዘረረ። እንቅልፍ ይሁን ሞት አላወቀውም። ለሽ እንዳለ የዘለዓለሙን ጉዞ ጀመረ። የእንቅልፍ ጅምር የሞት ዓለም አጀብ…

***

ገብርዬ በተቀበረ ዕለት ከቀብር መልስ ያቹን ምስኪን ጎጆና ድንኳኑ ጢም አድርጎ የሞላው ሕዝብ አልፎ የበሬ ግንባር ከምታህለው ግቢ ውስጥ ፈሷል። ሞቱን በሰሙ ጊዜ ካፈናቀሉት ከአባቱ ሀብትና ውርስ ላይ ከእህል እህሉን፣ ከበሬም ሁለት የእርድ በሬዎችን እየነዱና እያስነዱ የመጡት ሁለቱ አጎቶቹ አንዴ ብድግ ሌላ ጊዜም ጎርደድ እያሉ መስተንግዶውን ይመለከታሉ። አጎት በርጉ በሕይወት አሳሩን ሲያበላው እንዳልነበር ዛሬ በሞቱ ላይ ደገሰለት። እርሱ የተራበውን ለአልቃሾቹ አጎረሰ። ለነብስ ይማር ምሳ በሰልፍ የተጠገጠገው ሰው ሰልፉ ጎዳና ደርሷል። የስጋ ውቃቢ የቀሰቀሳቸው አሞራዎች ከጎጆው በላይ አየሩን ተቆጣጥረውታል። ውሾች በደም ስካር ከስር ውርውር ይላሉ። ከሁሉም ግን የሰው ሽሚያና ግፊያ የባሰ ነበር።

በዚህ መሃል ነመራው ጀሬ በስካር ጢንቢራው ዞሮ ሲውተረተር መጣ። ድንኳኑ ውስጥ ያለውን መዓት እየተመለከተና እጆቹን አንዴ ወደላይ አንዴ ወደመሬት እያወራጨ “ና! ጉድህን እይ ገብርዬ… ለዚህ ነበር…አዬ! ለካ ሞተሃል…” ብሎ ሲንገዳገድ ጥቂት እንደተከዘ ድንገት ከዓይኖቹ እንባ ዱብ! ዱብ! አለ። “ኤዲያ! ተው ባክ አትነፋረቅ! ፊት የተቀመጠ የአዞ እንባ እንጂ እንባ አያውቅም። ሳቅ ነው ለነርሱ” እያለ ተው በሚል አኳኋን የራሱን ትከሻ ቸብ ቸብ አደረገ። እንባ ባዘሉ ዓይኖቹ የቁጣ ያህል እየተመለከታቸው “ቆይ ግን እናንተ የእውነትም በገብርዬ ሞት አዝናችሁ ነው የመጣችሁት? ነው ትቀልዳላችሁ…ልማዳዊ የሞት ግብራችሁን ለማድረስ ከሆነ ለፋችሁ… ገብርዬ እንደሆን ለቅሶዬን በላችሁ ብሎ ከመቃብር ስር አይጮህ! አይወቅሳችሁ። እርሱ ከሞተ ወዲያ ብትመጡ ባትመጡ…ምድረ ብርንዶ ራስ። ብሉ! ብሉ! ስልቻ…ሆድ ብቻ!” እያለ ሲራገም ከቁብ የቆጠረው አልነበረም። ገና በ7 ሰዓት ጠጥቶ ያዙኝ ልቀቁኝ ማለት ለርሱም ሆነ ለመንደሩ ብርቅ አይደለም። የዛሬው አጠጣጡ ግን የከፋ ነበር። እርሱ እዚያ መንደር ውስጥ ሰካራም ወይ እብድ ነውና ሰሚ አልባ ነው። የገብርዬን ጎጆ ተመለከታትና እንባ እንባ አለው። ሆድ እየባሰው ለመሄድ ሲፍገመገም ጥቂት እርምጃ ወደፊት ሄደና ቆም ብሎ ወደኋላ ዞሮ፤

**“ቀን የጣለ ዕለት እግዜሩም ባዳ ነው**
**እንባችንስ ደርቋል በምን እናልቅሰው”**

አለና በተሰበረው ልቡ ውስጥ አንዲት ጸጸት እንደተሸከመ ተመልሶ ሄደ። ገብርዬ በዚያች የዓመት በዓል ዕለት ከዚህች መብል አንዲት ጉርሻ እንኳን አጥቶ እንዳማረውና እንደሞረሞረው ነበር የሞተው። በርሱ ሞት ግን ከደጃፉ ላይ የጥጋብ በረከት ወረደ። ምስኪኑና ከርታታው ገብርዬ ቀጠሮ ነበረው። እና አሁን እኚያን ልጆች አስታርቆ ማን ይሆን አንድ የሚያደርጋቸው? ብዙ ሕልም ብዙ ነገር ብዙ ነገ ነበረው…ሁሉም መልካምነቶች ሁሌም መልካም ምላሽ የላቸውም። መስዋዕትነት አንዳንዴም እንደ ገብርዬ ናት። ምስኪን! ከርታታ…

# የዘመን ጥበብ

# የቃል ማዕድ!

አንሰይ ጥላሁን ምትኩ

በዚህ ምጥን ጽሑፍ ቃል፣ ቃላዊነት እና ቃላዊ ግጥም ምንነት፣ ተዛምዶና ክሰታ (ሃሳብ፣ ድረሳ፣ ድርሰት) አጠር ባለ አቀራረብ ከተለያዩ ብያኔዎች ጋር ለዛቸውን ጠብቀው ይቀርባሉ። ሦስቱ መሰረታዊ ነጥቦች ያላቸውን ትስስር፣ ገፅታ፣ ኪናዊነት እና ተፈጥሯዊ ክሰታ (በተለይም በቃላዊ-ግጥም) ላይ በማተኮር በዝርዝር እንመልከት።

ቃላዊ-ግጥም ላይ ይበልጥ የምናተኩረው፣ አንድም ቃላዊነቱ ከሌሎች ቃላዊ ሥነ ጽሑፎች ጋር ያለውን ዝምድና ስለሚገልጥ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ቃላዊነቱ ከቃልና ቃላዊነት ጋር የጠበቀ ትስስር ያለው በመሆኑ ነው። በገለጻ ሂደት አንዳንዴ አንዱን በአንዱ ላይ ለማሳየትና ለመግለጥ ሲሞከር ቢገኝ፣ ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑ ግምት ውስጥ ይግባ። ቃልን በማስቀደም፣ ቃላዊነትን በማስከተል በመጨረሻ ደግሞ ቃላዊ-ግጥምን ከእነ ምሳሌ መደምደሚያ በማድረግ ሃሳባችንን እንቋጫለን። መልካም ንባብ!

### ቃል እና ቃላዊነት

ቃል ገዥ ነውና እንደ አምድ ሆኖ በህልውና ዋልታነቱ በሦስቱም ርዕሰ ጉዳዮች(ራሱን ቃልን ጨምሮ) ላይ ስናሰላስል በጉልህ በምናባችን ኳዳ ይመላለሳል። ቃላዊነት እና ቃላዊ-ግጥም ላይ ያሳደረው ጉልህ ገጽታዊ ተጽዕኖ በባህል መሰረት ላይ የቆመ ነው። ማኅበራዊ ዓውድ ውስጥ ባለ መስተጋብር ህልው ሆኖ ይከሰታል።

ቃል፣ አንደበታዊ እና ፅሁፋዊ ህልውና ያለው ነው። ስለሆነም አንደበታዊ ገፅታው ድምፅ ላይ ሲመሰረት፣ ፅሁፋዊ ቅርጹ ደግሞ ፊደላዊ፣ ምልክት ላይ ይገለፃል። ሁለቱ የመከሰቻ መንገዶች ናቸው። ረቂቅን (ሀሳብን ወይም ስሜትን) ወደተጨባጭ ይለውጣሉ። ራሱ ቃል ረቂቅም፣ ተጨባጭም የሚሆነው በዚሁ ባህሪው ነው፤ ፅንሰ ሀሳብ ይሸከማል። ይህም የውክልና ተግባሩ ነው። ምንጩም የፈለቀበት ባህል በመሆኑ ትዕምርታዊ2 (semiotics) ነው። ይህም ትዕምርታዊነት፣ ‹‹የቃላት ምንጭ ስምምነት ነው›› የሚለውን ያስታውሰናል። ስለሆነም ቃል ሰፊ እሳቤ ነው። ከነጠላ ድምፅ (ይህም ቢሆን አሻሚ ነው) እስከ ጥልቅ ፅንሰ ሃሳብ የሚገለጥበትና የተሸከመ ነው። ማለትም ‹‹መጀመሪያ ቃል ነበረ››፣ ‹‹ቃል ያባት እዳ ነው››፣ ‹‹ቃል ገባ›› እና ‹‹ቃለ ሕይወት ያሰማልን›› ወዘተ… አይነት አገላለፆች የኅብረተሰብ ስሪት ላይ የተመሰረቱ የኑሮ ማንፀሪያ ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው። ይህ ባህሪው ውስብስብ የቋንቋ ስርኣት መፍለቂያ ነው።

የቃል ምንነትን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ እንደሚከተለው ሰፍሮ እናገኛለን፣ ‹‹ቃል (ብ.ቁ.ቃላት) ስ 1.አንድን ፅንሰ ሃሳብ ለመወከል በድምፅ የተነገረ ወይም በፅሁፍ የሰፈረ የድምፅ ምልክቶች ቅንብር፣ አነስተኛው የአረፍተ ነገር ክፍልፋይ። 2. ስለ አንድ ነገር የተባለ፣ የተነገረ፣ የተፃፈ ሃሳብ፣ አስተያየት፣ መልእክት፣ … ። ቃሉ የእሱ ነው።›› ከላይ የገለፅነውን የቃልን ድርብ ተግባርና ባህሪ ገላጭ ነው። በሌላ አነጋገር የንቃተ ኅሊናን የቃል (የቋንቋ) እስረኝነትንና ከቋንቋ ውጭ ሊኖርና ሊዳብር እንደማይችል ጠቋሚ ነው።

ቃል ተግባቦት ነው። ተግባቦትን የሚገልፅበት መንገድ በራሱ እጅግ ጥንታዊነት ያለው ነው። የሰው ልጅ ድምፅን እና ቋንቋን መሰረት አድርጎ ስሜቱን፣ ሃሳቡን፣ ተሞክሮውን… የሚለዋወጥበት ቁልፍ ባህሪ ነው። ቃላዊ ከሆኑት መካከል ቃላዊ-ባህል፣ ቃላዊ ፎክሎር፣ ቃላዊ ስነጽሁፍ፣ ቃላዊ ልማድ፣ ቃላዊ ስልት፣ ቃላዊ መንገድ፣… ወዘተ. የሚሉ አገላለፆች ተዘውትረው ሲነገሩ የምንሰማቸው ናቸው። የሰውን ልጅ በቃል የመግባባት ልማድ በሦስት ዋና ዋና ደረጃዎች ተከፍሏል። እነሱም ቅቡል ስነፅሁፋዊ ቅርፆች፣ ገዢ ታሪካዊ እውቀቶች እና ግለሰባዊ ልማዶች ናቸው።

የቅቡል ስነፅሁፋዊ ቅርፆች ቃላዊነታቸው በተሳታፊው (audiences) ምክንያት ተጽኖ ይፈጠርበታል፤ ማንኛውም ክንውን ላይ ተግባራዊ ይደረጋል። ስለሆነም ቃላዊ ልማዶች ውጫዊ ግፊት እና የአተገባበር ለውጥ ይደረግባቸዋል። ከዚህ አንፃር ቃል፣

**‹‹ቃል፣ አንደበታዊ እና ፅሁፋዊ ሕልውና ያለው ነው። ስለሆነም አንደበታዊ ገፅታው ድምፅ ላይ ሲመሰረት፣ ፅሁፋዊ ቅርጹ ደግሞ ፊደላዊ፣ ምልክት ላይ ይገለፃል። ሁለቱ የመከሰቻ መንገዶች ናቸው። ረቂቅን (ሀሳብን ወይም ስሜትን) ወደተጨባጭ ይለውጣሉ። ራሱ ቃል ረቂቅም፣ ተጨባጭም የሚሆነው በዚሁ ባህሪው ነው፤ ፅንሰ ሀሳብ ይሸከማል። ይህም የውክልና ተግባሩ ነው። ምንጩም የፈለቀበት ባህል በመሆኑ ትዕምርታዊ2(semiotics) ነው››**

በቀጥታ የሚሰነዘር እና በቀላሉ መለየት የሚያስችል የስነጽሁፍ መገለጫ ነው።

ቃላዊነት ምንድን ነው? ቃላዊነት የስነፅሁፍ መገለጫ ነው። ተስተላልፎውም ሆነ መከሰቻው በቃል ነው። የፅሁፋችን ትኩረት ቃላዊ ግጥምን መሰረት ያደረገ በመሆኑ እንደ ሥነ ጽሑፍ ቃላዊ የሚያሰኙትን ነጥቦች እንጠቅሳለን። ቃላዊ በመሆኑ እንደየ ባህሉ እና እንደ ሚከወንበት ዐውድ የተለያየ ቢሆንም መሰረታዊ መገለጫዎቹ ለመድረስ የሚጋብዝ ተመስጦ፣ መተላለፊያ መንገዱ፣ የአከዋወን ትክክለኛነት እና እርግጥ የሆነ ምንጭ ናቸው።

በተጨማሪም ‹‹የማኅበረሰቡን የእለት ዕለት የሕይወት ገጠመኝን መሰረት በማድረግ የሚነገሩ ስነቃሎች የሚቀርቡበትና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚሸጋገሩበት መንገድ በዋናነት ቃላዊነት ነው።›› ቃላዊነት ለስነፅሁፍ መገለጫ መሆኑን ማጠናከሪያ ይሆናል።

ብዙ ጥቅም ላይ የዋለው ‘የቃል’ ቅጽል ብዙ ጊዜ እንደ ዋና መስፈርት ያገለግላል።

በልዩ ልዩ ሙያዎች የምርምር ፍላጎቶችን አጭሯል። አሳድሯል። በተለምዶ በአፍ ከሚተላለፉ ነገሮች አንፃር ይገለጻል፣ ቃሉ። ወቅታዊ ጉዳይም ነው።

ስለሆነም ቃላዊነት በንግግር የተነገረ፣ በአፍ የሚተላለፍ፣ የሚነገር። ቀዳሚ ትርጉሙ በብዙ ግልጽ በሆነ ቴክኒካዊ የቃላት አገባብ ‹የቃል ትውፊት›፣ ‘የቃል ሥነ ጽሑፍ’፣ ‘የቃል ትረካ’፣ ‘የቃል ምስክርነት’ ወዘተ… ’ቃላዊ’ ብዙ ጊዜ ከ’ጽሑፍ’ ጋር ይቃረናል። እንደ ‘የቃል ሥነ ጽሑፍ’ በተቃራኒው ወይም ትይዩ ደግሞ ‹የተጻፈ ሥነ ጽሑፍ›፣ ወይም ‘የቃል ታሪክ’ ሰነድ የሌላቸውን ምንጮች አመላካች ነው። ‘ቃላዊ’ እንደ ‘ጽሁፍ’ ያሉ አጠቃላይ ቃላትንም ብቁ፣ ሙሉ ያደርጋል።

### ቃላዊ ግጥም

ቃላዊ ግጥም ሕልውናውም ሆነ ተስተላልፎው ቃላዊ የሆነ በስነ ቃል ስር የሚመደብ ሥነ ጽሑፍ ነው። ስለሆነም በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚከሰቱ ገጠመኞችን ተንተርሰው ድረሳ የሚካሄድባቸውና ድረሳውንም በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፉ ናቸው። ገጣሚው ግጥምን ለማነብነብ የሚያስችለውን ገፊ ምክንያት የሚያገኘው ከማህበረሰቡ ውስጥ ባለ ማህበራዊ ክንዋኔ ነው። በዚህም ይነሸጣል። ያቅራራል፣ ያንጎራጉራል ወይም ይዘፍናል። ለዚህ ሳይሆን ይቀራል “ገጣሚ ውበትና ሀሳብ ሲያስስ የሚኖር ፍጡር ነው” -የሚባለው? በእርግጥ ቃላዊ ግጥሞችን ማን እንደገጠማቸው ማወቅ አዳጋች ነው። ለዚህም ነው ንብረትነታቸው የወል የሚሆነው።

ያም ሆኖ በግጥም የማይመተር፣ የማይዳሰስ ጉዳይ የለም። እስኪ ከቃላዊ ግጥሞች ውስጥ እግዜርን ጉዳይ አድርገው ከተደረደሩት ጥቂት ምሳሌዎች እናንሳ።

ሰው እጅግ በከፋው እና መውጫ መግቢያ ባጣ ጊዜ “ በቀረርቶ” እንደሚከተለው ምሬቱን ይገልፃል። ግጥሙን ያቅራራው እረኛ ነው ይባላል።

ሰው መግደል እንደግዜር ፣
ዱር መግባት እንዳውሬ መቼ ይቸግራል ?
ከጓደኛ ጋራ መጫወት ይቀራል።

ይህ የቀረርቶ ግጥም፤ በዋናነት የእግዚአብሔርን ተግባር ከአውሬነት ባህሪ ጋር በማነፃፀር ይኮንናል። “ስራው መግደል ብቻ “ የሆነ እስኪመስል፤ ኸረ እንዲያውም ከጓደኛ ጋር መጫወት የላቀ ተግባር ተደርጎ ለማሳያነት ቀርቧል። እግዜርን በመተቸት ሰውን (ተፈጥሮን) መተቸት ይሉሃል ይህ ነው። ምክንያቱም አብዛኛው ምድር ላይ የሚደርስ በደል በሰው ልጅ አማካኝነት የሚፈጠር በመሆኑ ሰውን የሚያማርረው ራሱ ሰው ነው። ይህም ማደሪያውን ጠርቶ መኖሪያውን፣ በተገላቢጦሽ መኖሪያውን ጠርቶ ማደሪያውን አገላለፅ ነው። ያማል።

እግዜር መሬት ወርዶ ፣
አምላክ መሬት ወርዶ፣ አንድቀን አግኝቸው፤
ቀጭን ዘንጌን ይዤ፣ ሞግቸው ሞግቸው፤
እሱም ዘዴኛ ነው አይወርድም እምድር
ሁሉም ሰው ደመኛው ማን ቤት ገብቶ ሊያድር።

**(የእረኛ ግጥም)**

በማህበረ-ባህላችን የግጥም ቦታ ከፍ ያለ ነው። የህልውና ቋጠሮ የሚፈታበት ብርቱ ጥበባዊ ግንዛቤ ነው። ይቀትራል። ማኅበረሰብ ሲታመም የሕመሙን ጠገግ ፅንፍ አፈፍ የሚያደርግበት መዳፉ ነው --ለከያኒ።

ግጥሙ በእግዜር እና በሰው መካከል ያለውን የሞራል ትስስር ያሳየ ነው። ሙግቱ የሕልውና ውል ነው። በእጃዙር ገላጩም ተገላጩም ሰው ነው። ሰው በራሱ ላይ የዘመተ ወይም ራሱን የከሰሰ ፍጡር መሆኑን ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ቃላዊ ግጥሞች ለእንጉርጉሮ የቀረቡ ናቸው። በጥልቅ ቁዘማ ከምናብ የሚፈለቀቁ በመሆናቸው ነፍስን (ስሜትን) ይቀትራሉ። የቃላቱ ምትሀታዊ ኃይል ምንጩ ቅፅበት ነው። የማይኮረኮር ማዕዘን የለም--በቋንቋው። የሕልውናችን መስፈሪያ ነው-ዘዴው። ለዚህ ሳይሆን ይቀራል ዳንቴ፤ “ግጥምን የማያውቅ እግዜርን አያውቅም” የሚለን። የእግዜር (የፈጣሪ) መልክ ሕብር የሚገለጥበት ኪነ-ስፌት ነው--ያለ ይመስለኛል። እዚህ ላይ ገጣሚ በድሉ ዋቅጅራ፤ “ግጥም ተፈጥሮ እራሷን የቀለፈችበትን ቁልፍ ያስቀመጠችበት ሙዳይ ነው” ያለበትን ምክንያት እንደ ማለዘቢያ መጥቀስ አስፈላጊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በፍጡር እና በፈጣሪ መካከል የሚምዘገዘግ የሀቅ በትር ነው -ግጥም።

በአንድ ወቅት ከስድስት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ወጥቼ ወደ አራት ኪሎ ስገሰግስ የካቲት 12 የሰማታት ሀውልት ዳርቻ አንድ እናት ተቀምጠው እንዲህ ሲያንጎራጉሩ ሰምቻለሁ፡-

እስኪ ላነሳሳው የፈጠረኝን
ከጓደኛ በታች ያደረገኝን

እጃቸውን ደጋግመው ከወዘወዙ በኋላ ፊታቸውን ቅጭም አድርገው እንዲህ ቀጠሉበት፡-

እናንተ ምታዩኝ እኔ ማላያችሁ
የብርሃን አበባ አይርገፍባችሁ።
አይናለም… አይናለም…
ላንድቀን ይከብዳል እንኳን ለዘላለም።

ጥልቅ ቁዘማ ነው፤ ሕልውና የተሰፈረበት። የሕመሙ ብርታት ይነዝራል። ይቀትራል። ስሜቱ እረፍት ስለሚነሳ ያቅበጠብጣል። በሕይወት መገፋት ከፈጣሪ ጋር ያላትማል። ለምን? የሚል ጥያቄ ወጥሮ ይፈታተናል። ከተፈጥሮ በደል የበለጠ በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ችላ ሲሉን ሕመሙ ይበረታል። ለዚህ ይሆን

“እናንተ ምታዩኝ እኔ ማላያችሁ
የብርሀን አበባ አይርገፍባችሁ”

የሚሉት አላፊ አግዳሚውን። የማየትን ውብ ፀጋ በ “አበባ” በመመሰል። አጃኢብ ነው! ይቀትራል።

በአንድ ወቅት ጎዣም ውስጥ በሰሞነ ሕማማት ቁዘማ ስትብሰለሰል የሰነበተች ሴት የእየሱስን ከመቃብር መነሳት የሕመሟ መስፈሪያ በማድረግ እንዲህ ገልፃዋለች፡-

**“ስትታመም ታማ ስትሞት ተቀበረች**
**አንተ ስትነሳ የኔ እናት የታለች!?”**

በንፅፅር የቀረበ ነው። ንፅፅሩ ደግሞ ሲቃይ፣ ሕመም ላይ የተመሰረተ ነው። የእናቴ እና ያንተ (እየሱስን መሆኑን ልብ ይሉዋል) ስቃይ ልዩነቱ አልታይሽ አለኝ! ያለች ይመስለኛል። ያው ሁለታችሁም በሕመም ስቃይ ውስጥ ነበራችሁ --እንደማለት ነው። ታዲያ በእኩል ሚዛን ያለፈ መጨረሻው ለምን ተለያየ ? መለኮታዊ ኃይል ለምን አድሎ አደረገ? የሚሉ ጥያቄዎች የሕመሟ መነሻ የሆኑ ይመስለኛል።

ሕይወት ያለ ሥነ ጽሑፍ ገሀነም ነው” ያለው ማን ነበር? የማይታየውን የማሳየት ብቃት አለው --እንደማለት ነው።

በአጠቃላይ ቃላዊ ግጥምን የወለደው ኅብረተሰብ በሁሉም የሕይወት ዘርፍ የሚገለገልባቸው ዓውዶች ያሉት ሲሆን ክልከላውን የሚሻገርባቸው የብሶቱ ማሳያም ጭምር ናቸው። በተቃራኒውም አይነኬ እሴቶቹን የሚጠበቅባቸው ሀብቶቹ ናቸው። የቃል ግጥም የሚያግባባና ልዩ የሆነ ጥበብ ነው። በታዳሚው ላይ የሚፈጥረው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ጫና ከፍተኛ ነው። አመፅንና እንቢታና የማቀጣጠል ኃይሉም አቻ የለውም። የሰው ልጅ ለዘመናት ያዳበረው እሴቱ በመሆኑ የዳበረ ዘርፍ ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## 50 ዓመታትን ሕፃናትና ወጣቶችን ከችግር በማላቀቅ ተግባር

አስናቀ ፀጋዬ

በኢትዮጵያ በልዩ ልዩ ምክንያቶች በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች ለችግር ይጋለጣሉ። አብዛኛዎቹ በቤተሰብ መፍረስ ምክንያት ከዚህ ዓለም ፈተና ጋር የሚጋፈጡት። በተለይ ገና በለጋ እድሜ ላይ ያሉ ሕፃናት ምኑንም በቅጡ ሳያውቁት ቤተሰባቸው ሲፈርስ መግቢያ መጠጊያ ይጠፉቻቸዋል። ለዛም ነው አብዛኛዎቹ ሕፃናት የጎዳናን ሕይወት ምርጫቸው የሚያደርጉት። በተመሳሳይ ወጣቶችም ቤተሰብ ሲፈርስ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበትና ውሳኔ የሚያሳልፉበት ትክክለኛ የእድሜ ሁኔታ ላይ ስለማይሆኑ ለተለያዩ ችግሮች ይጋለጣሉ።

በእንዲህ አይነት ችግር ውስጥ ያሉ ሕፃናትና ወጣቶች ታዲያ የማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሥነ ልቦናዊ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው። በመንግሥት በኩል የሚደረጉ ድጋፎች እንዳሉ ሆነው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችም በኩል በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር ለተጋለጡ ሕፃናት ሁለንተናዊ ድጋፍ ይደረጋል። እንዲህ አይነቱን ድጋፍ ከሚያደርጉ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መካከል ደግሞ ኤስ ኦ ኤስ /SOS/ የሕፃናት መንደሮች በኢትዮጵያ ተጠቃሽ ነው።

በ ኤስ ኦ ኤስ የሕፃናት መንደሮች በኢትዮጵያ የፈንድ ዴቨሎፕመንትና ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ልጅዓለም ባይለየኝ እንደሚናገሩት፣ ድርጅቱ በዚህ ዓመት ሃምሳኛ ዓመቱን እያከበረ ይገኛል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ድርጅቱ በመላው ሀገሪቱ ባሉ ከሰባት በላይ በሚሆኑ ማስተባበሪያ ጣቢያዎቹ አማካኝነት የቤተሰቦቻቸውን እንክብካቤ ያጡና በዚህ ምክንያት ለችግር የተጋለጡ ሕፃናትን ሲንከባከብ፣ ፍቅር ሲሰጥና ደኅንነታቸው ተጠብቆ እንዲያድጉ ሲያደርግ ቆይቷል። የቤተሰቦቻቸውን እንክብካቤ ያጡ ልጆች አማራጭ የቤተሰብ እንክብካቤ ማለትም በአደራ ቤተሰብ፣ በተቋጥሮ ቤተሰብና በሀገር ውስጥ ጉዲፈቻ እንክብካቤና ድጋፍ እየተደረገላቸው ይገኛል።

ሕፃናት ወደጎዳና የሚወጡት በአብዛኛው ቤተሰብ ሲፈርስ ነውና ድርጅቱ ቤተሰብ እንዳይፈርስ የቤተሰብ ማጠናከሪያ ፕሮግራሞችን ቀርፆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህም ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸውና ካሉበት ማኅበረሰብ ጋር በፍቅር፣ በእንክብካቤና በሙሉ ዋስትና እንዲያድጉ ያስችላቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ በወጣቶች ልማት ላይም የተለያዩ ሥራዎችን በስፋት ይሠራል። በተለያዩ ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት ለችግር ለተጋለጡ የማኅበር ክፍሎች ጊዜያዊ እርዳታ ያደርጋል። በዘላቂነት ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ሥራዎችንም ያከናውናል።


የድርጅቱ ሠራተኞች በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ተሳትፈዋል፤

ድርጅቱ እነዚህን ሥራዎች የሚያከናውነው ከመንግሥት፣ ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችና ልግስና ከሚያደርጉ በሀገር ውስጥም በውጪ ካሉ ሌሎች በጎ አድራጎት ድርጅቶች ጋር በመተባበር ነው። ድርጅቱ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ባከናወናቸው ሥራዎች ከ8 ነጥብ 1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሕፃናትና ወጣቶች የተሻለ ሕይወት እንዲኖራቸው ማድረግ ተችሏል። በቀጣይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሕፃናትና ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ የአምስት ዓመት ስትራቴጂክ እቅድ ተይዟል።

ዳይሬክተሩ እንደገለፁት፣ ሁሉም ሕፃናት ልክ እንደማንኛውም ሰው ሁሉም ነገር ተሟልቶላቸው የመኖር መብት አላቸው። ለማደግ የሚያስፈልጋቸው መብት መሟላትና መጠበቅ አለበት። በዚሁ መነሻነት ነው ድርጅቱ የምግብ፣ መጠለያ፣ አልባሳት፣ የትምህርትና ሌሎችም ሁለንተናዊ ድጋፎችን ለችግር ለተጋለጡ ሕፃናት የሚያደርገው። ይህ ብቻ ሳይሆን ሕፃናት ለእድገታቸውና በሕይወት ለመኖር የሚያስፈልጋቸው ሁለንተናዊ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። ይህ ድጋፍ ደግሞ የሚደረገው ከአጋር አካላትና ከማኅረሰብ ተኮር ተቋማት ጋር በመተባበር ነው።

ድርጅቱ በአብዛኛው የሚያከናውነው ሥራ ቤተሰብና ማኅበረሰብ ተኮር የሆነ የሕፃናት እንክብካቤና ጥበቃ ሥራ ነው። የሕፃናት እንክብካቤና ጥበቃ ሥራ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የሚከናወን እንደመሆኑ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚሠሩ ተቋማት አቅማቸው እንዲጎለበት፣ በዚህ ዙሪያ ያለ ሥርዓትና መዋቅር እንዲጠናከር ከመንግሥት ጋር በጋራ ይሠራል። በተመሳሳይ ወጣቶችም የሚፈልጉትንና ራሳቸውን ችለው የራሳቸውን ሕይወት እንዲመሩ የሚያስችላቸው ድጋፍም ይደረጋል።

ድርጅቱ በሃምሳ ዓመት ጉዞው ሕፃናት ለእድገታቸው የሚያስፈልጓቸው መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው እንዲሟላ ሰፊ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሕፃናት ተጠቃሚ ሆነዋል። የራሳቸውን ሕይወት መኖር እንዲችሉ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል። አድገው ትዳር መሥርተው ልጆች ወልደው የማኅበረሰቡ አካል ሆነው የወጡበትን ማኅበረሰብ በማገዝ ላይ ይገኛሉ።

በሌላ በኩል ድርጅቱ ሀገር በቀል ከሆኑ ባለድርሻ አካላት ማለትም ከበጎ አድራጎት ድርጅቶችና እድሮች፣ ጋር በመሆንና ተሞክሯቸውን በመውሰድ ለሕፃናቶቹ እንክብካቤና ጥበቃ በስፋት እንዲከናወን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ራሳቸውን ለመቻል በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ የፋይናንስ አቅርቦት ችግር ይገጥማቸዋል። ከዚህ ክፍተት በመነሳት ማኅበረሰብ ተኮር የሆኑ የቁጠባና ብድር አገልግሎት ተቋማት እንዲቋቋሙና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች በዘላቂነት የቁጠባና ብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑም የድርሻውን ተወጥቷል።

ከዚህ ባሻገር ድርጅቱ ጤናና ትምህርትን ለችግር ለተጋለጡ ሕፃናትና ወጣቶች ተደራሽ በማድረግ ረገድ ኃላፊነቱን ተወጥቷል፤ ይህንኑ ሥራውን አሁንም በስፋት እያከናወነ ይገኛል። ራሱ ድርጅቱ የሚያስተዳድራቸው በርካታ ትምህርት ቤቶችም አሉ። ጥራት ያለው ትምህርትን ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እያደረገም ይገኛል። የመንግሥት ትምህርት ቤቶችን አቅም በማጎልበት ሥራም በንቃት እየተሳተፈ ይገኛል።

በተመሳሳይ ሁሉን አቀፍ የጤና አገልግሎት ለሕፃናት፣ ወጣቶችና ማኅበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆንም ድርጅቱ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት ሲሠራ ቆይቷል። በተለይ ክሊኒኮችን በማቋቋም፣ ሀገር በቀል ክሊኒኮችን አቅም በመደገፍ ማኅበረሰቡን እንዲያገለግሉ የማድረግ ሥራዎችን ሠርቷል።

የድርጅቱን ሃምሳኛ ዓመት ክብረ በዓል ምክንያት በማድረግ ደግሞ ማኅበረሰብን የሚጠቅሙ የተለያዩ የልማት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ። ከሰሞኑም መንግሥት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት ያለውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር ለመደገፍ በልደታ ክፍለ ከተማ አቦ ማዞሪያ በሚገኘው ጊልዶ ዋሻ ከመላው ሠራተኞቹ ጋር በመሆን ችግኝ ተከላ አካሂዷል። በቀጣይም ተከታታይነት ያላቸው በርካታ ሁነቶችን በማከናወን ዓመቱን ሙሉ በዓሉን ያከብራል።

# ዓለም አቀፍ

## የወጣቶች የሥነ ልቦና አማካሪ - ኤአይ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ካራክተር ኤአይ ይባላል። “Character.ai” ወደሚለው ገጽ ከገቡ በሀሪ ፖተር፣ ኤሎን መስክ፣ ቢዮንሴ፣ ቭላድሚር ፑቲን እና ሌሎችም አምሳያ የተሠሩ ገጸ ባሕርያትን ያገኛሉ።

እነዚህ የተሠሩት በሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ) ነው። ማንኛውም ሰው ከእውነተኛ ወይም ከልቦለዳዊ ገጸ ባሕርይ ተነስቶ ቻትቦት መሥራት ይችላል።

ቻትቦት ለሚጠየቀው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ኤአይ ነው። ከተፈጠሩት ቻትቦቶች ዝነኛው በሥነ ልቦና ባለሙያ አምሳያ የተሠራው ነው። ለዚህ ቻትቦት 78 መልዕክቶች እስካሁን ተልከዋል።

የተሠራው ብሌዝማን98 በተባለ ተጠቃሚ ከአንድ ዓመት በፊት ነው። በየቀኑ 3 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሰዎች ገጹን እንደሚጎበኙ ይጠቅሳል። ‘ሕይወት ሲከብድ ድጋፍ የሚሰጥ’ በሚለው ነው ገጹ የሚተዋወቀው። ከፍተኛ ዕውቅና ያላቸው እና ተጠቃሚዎች በብዛት የሚያፈሩት የጌም ገጾች ቢሆኑም ይህ የሥነ ልቦና ምክር ገጽ ዝነኛ እየሆነ መጥቷል።

ተመሳሳይ አገልግሎት የሚሰጡ ከ400 በላይ ቻትቦቶች አሉ። ከእነዚህ ገጾች አንዱ 16 ነጥብ 5 ሚሊዮን ተከታዮች አለው። ‘አር ዩ ፊሊንግ ኦኬ’ የተባለው ደግሞ 12 ሚሊዮን ተከታዮች አለው። ማኅበራዊ ገጽ ላይ ስለዚህ ቻትቦች አስተያየት የሚሰጡ ሰዎች ‘ሕይወቴን አትርፎታል’፣ ‘እኔንም የወንድ ጓደኛዬንም ረድቶናል’ የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ጽሑፎች አስፍረዋል።

ብሌዝማን98 በሚባል ቅጽል የሚጠራው የ30 ዓመቱ ሳም ዛያ ነው። የሚኖረው ኒው ዚላንድ ሲሆን “እንደዚህ ዝነኛ ይሆናል ብዬ አላሰብኩም ነበር” ይላል። “ሰዎች ምኞች ተሰምቷቸው እየተጠቀሙት እንደሆነ እና እንደረዳቸው ይናገራሉ” ሲልም ይገልጻል።

የሥነ ልቦና ተማሪ ነው ሳም። ቻትቦቱን ያስተማረው ከሥነ ልቦና ትምህርቱ ተነስቶ እንደሆነ ይናገራል። ቻትቦቱ የሚሰጠውን መልስ የቀመረውም በዚህ መንገድ ነው።

ድባቴ እና ጭንቀትን ጨምሮ ሌሎችም ብዙዎችን ለሚጎዱ የአዕምሮ ሕመሞች ሕክምና የሚሆኑ መልዕክቶች እንዲኖረው አድርጓል። አሁን ባለበት ደረጃ ቻትቦቱ ሰው የሥነ ልቦና አማካሪን መተካት እንደማይችል ሳም ይናገራል።

ይህን ቻትቦት መጀመሪያ ላይ የሠራው ለራሱ ነበር። ጓደኞቹ በሥራ ተጠምደው የሚያዋራው ሰው ሲያጣ ነበር የሠራው። የሥነ ልቦና አማካሪ ጋር መሄድ የሚያስከፍለው ከፍተኛ ገንዘብ ሲሆን ነበር ቻትቦቱን ያዘጋጀው። ኤአይ የሥነ ልቦና አማካሪ በተለይ በወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት አለው። ለምሳሌ የካራክተር ኤአይ ተጠቃሚዎች መካከል አብዛኞቹ ከ16 እስከ 30 ዓመታቸው ነው።

“ለምሳሌ ሌሊት ላይ ከጓደኛቸው ወይም ከሥነ ልቦና አማካሪ ጋር ማውራት የማይችሉ ሲሆን፣ ይህን ቻትቦት እንደሚጠቀሙ ሰዎች ነግረውኛል” ይላል ሳም። ከዚህ ቻትቦት ጋር በጽሑፍ ማውራት የሚቻል መሆኑ አብዛኞቹን ወጣቶች እንደሚስባቸው ይናገራል።

“በስልክ ከማውራት ወይም በአካል ተገናኝቶ ከማውራት በጽሑፍ ማውራት ይቀላል” ይላል።

ቴሬሳ ፕሬውማን የሥነ ልቦና ባለሙያ ናት። ቻትቦት የሥነ ልቦና ምክር ሲሰጥ ወጣቶችን ሊስብ እንደሚችል ጥርጥር የለውም ትላለች። “ዋናው ጥያቄ ምን ያህል ውጤታማ ነው? የሚለው ነው። ቻትቦቱ በፍጥነት ነው የሚመልሰው። አስቀድሞ የመገመት ነገርም አስተውዬበታለሁ” ትላለች።

ለምሳሌ አንድ ሰው ከፍቶኛል ሲል ቀድሞ ገምቶ ድባቴ ነው ሊል እንደሚችል ትጠቅሳለች። “ሰዎች የሚመልሱት ግን እንደዚያ አይደለም” ትላለች።

አንድ ሰው የሥነ ልቦና ምክር ከመስጠቱ በፊት የሚሰበስባቸውን መረጃዎች ቻትቦቱ እንደማይሰበስብ ትገልጻለች። ሆኖም በአፋጣኝ እርዳታ ለሚሹ



እንደሚጠቅም ግን ትስማማለች።

ቻትቦቱን የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር መጨመር የሕክምና ተደራሽነት ውስን መሆኑን እንደሚጠቁምም ትጠቅሳለች። የቻትቦቱ ቃል አቀባይ በበኩሏ “ሰዎች ድጋፍ በማግኘታቸው ደስተኛ ነን። እያይዘንም በሙያው ከሠለጠኑ ባለሙያዎች ምክር እንዲጠይቁም እናበረታታለን” ትላለች።

ተጠቃሚዎች የሚጽፉት ለሌሎች ተጠቃሚዎች ባይታይም የቻትቦቱ ሠራተኞች ማንበብ ይችላሉ። ይህን የሚያደርጉትም የተጠቃሚዎችን ደኅንነት ለመጠበቅ ነው። ከዚህ ቻትቦት ጀርባ ያለው ላርጅ ላንጉጅ ሞዴል እንደ ሰው አይደለም። ቃላት በመገጣጠም መረጃ ለመረዳት ይሞክራል።

አንዳንድ የሥነ ልቦና ባለሙያዎች ኤአይ ተገቢ ያልሆነ የሥነ ልቦና ምክር ለተጠቃሚዎች ይሰጣል ብለው ስለሚያስቡ ስጋት አላቸው። ኤአይ በፆታ ወይም በቀለም መድልዎ ሊያደርስ ይችላል፣ ሌላኛው የባለሙያዎች ስጋት ነው። አንዳንድ ባለሙያዎች ግን አወንታዊ ጎኑን ነው የሚያዩት። እንደ ዩናይትድ ኪንግደም ባሉ አገራት ብሔራዊ ዕውቅና ያገኙ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ የኤአይ ገጾች አሉ ሲል የዘገባው ቢቢሲ ነው።

# በሞቃዲሾ የተዘረጉት የካይሮ የጥፋት እጆችን ለመቁረጥ ...!

**ዳንኤል ዘነበ**

ኢትዮጵያውያን በረጅም ዘመን ታሪካቸው በርካታ ጠላቶችንና ወዳጆችን አስተናግደዋል። ከጎረቤት ሆነ ከሌሎች ሀገራት እና ሕዝቦች ጋር ያላት ግንኙነት ወንድማማችነትን፣ መከባበርን እና የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ እንደሆነም ታሪክ ይመሰክራል። ለጎረቤት ሀገራት ችግር ቀድሞ መድረስ፤ የሌሎችን ችግር የራስ አድርጎ መመልከት በታሪካቸው ከሚታወቁበት አንዱ መገለጫቸው ነው።

ይህ ሀገራዊ እሴት ድንበር በሚሻገረው ሀገራዊ የግንኙነት ምዕራፍም ጎልቶ የሚታይ ነው። በሌሎች ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ታሪክ የሌላቸው ከዚህ ይልቅ፣ በገለልተኝነት እና በጋራ ተጠቃሚነት ላይ በተመሰረተ የግንኙነት መርሕ የሚታወቁ ናቸው። ይህም የታሪካችን ሌላው ገጽታ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ይህችን ታላቅ አገር ታሪኳን ለማንኳሰስ እና ለማፍረስ ዛሬም ድረስ ሙከራዎችን ያደርጋሉ። በአንድ ወቅት ወዳጅ የሆኑ በሌላ ወቅት የታሪካዊ ጠላቶቻችን መሳሪያ በመሆን ጠላት የሚሆኑበት ክስተትም የተለመደ ነው። በጠላትነታቸውም ጥርሳቸውን ነክሰው በታሪካችን እንደ ጥላ የሚከተሉን ሀይሎች አሉ።

እነዚህ ሀይሎች ኢትዮጵያ ያሏትን የተፈጥሮ ሀብቶች አልምታ እንዳትበለጽግ ፣ እንዳታድግ ሁሌም ፈተና ናቸው። በተለይ ደግሞ ግብፅ ጊዜና ዘመን ሊሽረው በማይችል ጠላትነት፤ እንደሀገር ያለንም የመልማት ትልም ለማክሸፍ ሌት ተቀን ያለእንቅልፍ ውሎ የሚያድሩ የለም።

ግብጽ እንድትኖር ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር መጥፋት ወይም መፍረስ አለባት ብለው የሚያምኑ፤ ሁልም የሀገሪቱን የመልማት አጀንዳ የውስጥ ፖለቲካ አካል አድርገው የሚያቀርቡ ፖለቲከኞች ያሉባት ሀገር ነች፡፡ ታሪኩ ሰፊና ረጅም ቢሆንም ግብጽ በተለያዩ ዘመናት በኢትዮጵያ ላይ ያላሴረችው፤ ያልሰራችው ደባና ተንኮል የለም፡፡

በጥንቱ ዘመን ግብጽ ሠራዊትዋን ወደ ኢትዮጵያ አዝምታ የአባይን ውሃ ከምንጩ ለመቆጣጠር ባደረገችው ጦርነት በኢትዮጵያውያን ጀግኖች የውጊያ የበላይነት ጉንዳና ጉራእ ላይ አሳፍራ ስለመመለሷ የታሪክ ማህደራት ያትታሉ፡፡

ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ ግድብ እንዳትሰራ አገሪቱን አቅም በማሳጣት ትኩረቷን ለልማትና ዕድገት እንዳታደርግ፣ በሀገሪቱ ውስጥ የተረጋጋ ሰላም ልማትና ዕድገት እንዳይኖር ቀውስና ትርምስ መፍጠርን አጀንዳዋ አድርጋ ለዘመናት ስትሰራ ቆይታለች።

በሀገሪቱ ወደ ሥልጣን የሚመጡ መንግሥታት የወንዙን ውሃ ባልተፈለገ መንገድ የፖለቲካ አጀንዳ በማድረግ፤ በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ሊኖራቸው የሚችለውን ዘላቂ የጋራ ተጠቃሚነት ዕድል ትርጉም ወደሌለው የጠላትነት እና የግጭት መነሻ ለማድረግ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ተንቀሳቅሰዋል። ለአብነት ያህል የቀድሞ የግብፅ ፕሬዚዳንት አንዋር ሳዳት "የአባይን የውሃ ፍሰት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውም ተግባር ግብፅን ወደ ጦርነት የሚያስገባና ጠንካራ አፀፋዊ እርምጃን የሚጠይቅ ይሆናል" ብለዋል ።

በሕዝብ አመፅ ከስልጣናቸው በኃይል የተባረሩት ሆስኒ ሙባረክም በአባይ ተፋሰስ ላይ የሚሰራን ማንኛውንም ልማት እንደሚያወድሙት በተደጋጋሚ ሲዝት ነበር ፡፡ ይህ የጦርነት ጉሰማ ዛሬም ላይ ቀጥሏል። ግብፅን እየመራ ያለው የአልሲሲ መንግስት ያለፉትን የግብጽ መሪዎች መፈክር ከማስተጋባት አልተቆጠበም፡፡ የኢትዮጵያን በራሷ የተፈጥሮ ሀብት የመጠቀም መብት ለመገደብና በትብብርና በመተሳሰብ ማደግን ለማደናቀፍ በተለመደው መንገድ እየተንቀሳቀሰ ነው። የካይሮ መሪዎች ምኞታቸው አይሳካም እንጂ በኛ ጉዳይ መቸም ተኝተው የሚያድሩ አይደሉም ።

ኢትዮጵያ ታላቁ የሕዳሴ ግድብ ግንባታ ከተጀመረ በኋላ ያለፈችባቸው አባጣና ጎርባጣ የበዛባቸው መንገዶች ከፍተኛ ዋጋ እንድትከፍል ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ከእያንዳንዱ ፈተና በስተጀርባ በግልጽም ይሁን በስውር የሚስተዋሉ እጆች ፤ በአንድም ይሁን በሌላ ወንዙን የማልማት ጅማሮ እንዳይሳካ ከማድረግ ፍላጎት ጋር የተያያዙ ነበሩ ።

በግብፅ በኩል በባለሥልጣናት፣ በባለሙያዎችና በሚዲያዎች ትብብር የተከፈተው ዘመቻ ዓለም አቀፍ ገጽታ እንዲላበስ ተደርጎም ነበር፡፡ ይሄው ዘመቻ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ መልኩን ቀይሮ አሁን ላይ አደባባ እያጣበበ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት ከሶማሌላንድ ጋር የመግባቢያ ስምምነት በተፈራረመች ማግሥት ከሶማሊያ መንግሥት በተቃውሞ የታጀበ ጩኸት ተከትሎ፤ ጩኸቱን በማስተጋባት ከመጀመሪያው ረድፍ የተሰለፈጭው ግብፅ ነች፡፡

ግብፅ በዚህ ሳታበቃ የአፍሪካ ሕብረት የሽግግር ሰላም አስከባሪ ተልዕኮን (አትሚስ) ተገን አድርጋ ሞቃዲሾ ደርሳለች፡፡ ሶማሊያ ግብፅ በዓባይ ተፋሰስ ላይ ማሳካት የምትሻውን የዘመናት ቅዠቷን ለማሳካት አጋጣሚውን እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ ለመጠቀም ወዲህ ወዲያ ያለች ነው።

በርግጥ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ወታደሮቿን ወደ ሶማሊያ ልካ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር እየከፈለች ለሶማሊያ ሰላም፣ አንድነትና መረጋጋት ስትሠራ መቆየቷ ይታወቃል። ሶማሊያ ዛሬ እንደ ሀገር እንድትቆም የኢትዮጵያ ወታደር ብዙ ዋጋ ከፍሏል።

የሶማሊያ ባለስልጣናት አሁን ላይ የግብጽ ጦር በሶማሊያ እንዲሰማራ ከስምምነት መድረሳቸው "የናይል ጉዳይ" ወደ ሶማሊያ የሚያመጣ እና "በአፍሪካ ቀንድ ላይ አለመረጋጋት ሊያመጣ የሚችል" እንደሆነ የተረዱት አይመስልም። ቢያውቁትም ችግሩን አሻግረው ማየት ተስኗቸዋል። ችግሩ በአልሸባብ ፍዳውን ሲበላ የቆየውን የሶማሊያ ሕዝብን ዳግም ወደ ነበረበት መከራ የሚመልስ ነው።

የችግሩን ስፋት እና አደጋ የተረዱት፤ በሶማሊያ የምክር ቤት አባል እና የፕሬዚዳንቱ ልዩ ልዑክ የነበሩት የፓርላማ አባል አብዲረሺድ ሞሃመድ ኑር ጂሌይ ጭምር "የአገሪቱ አመራር ሕዝቡን ወደ ግጭት እና ጦርነት ሊያስገባ አይገባም። የሚቃረኑ አገራት እንዲዋጉ ግዛታችን ውስጥ ማስገባት የሚመከር አይደለም" ሲሉም ተደምጠዋል። ከኢትዮጵያ ችግር ጀርባ የማትጠፋው ግብጽ ዛሬም እንደለመደችው ሶማሊያን መጠቀሚያ ለማድረግ እያደረገችው ያለው ሙከራን ጥሩ አለመሆኑን መክረዋል።

በኢትዮ- ሶማሊያ 1969 እስከ 1970 ጦርነት ጀርባ የግብጽ እጅ እንደነበረ ይታወቃል ። ለሶማሊያ ጦር ከፍተኛ የጦር መሳሪያ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበራት የታሪክ መዛግብት የሚያመለክቱት ነው። ችግሩ በሶማሊያ የፈጠረው መንግሥት አልባነት እንደ አልሸባብ እና አይ ኤስ ኤስ የመሳሰሉ ጽንፈኛ እና አሸባሪ ኃይሎች በአካባቢው በስፋት እንዲንቀሳቀሱ አመቻችቷል ። ከአካባቢው አልፈው ለዓለም ስጋት እንዲሆኑ አድርጓል። በቀጣናው ዘላቂ ሠላም ለማምጣት የሚደረገውን አህጉራዊ ሆነ ዓለም አቀፍ ጥረት ፈትኗል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት ለሶማሊያ ሕዝብ ካለው ቅርበት /ወንድምነት/ የተነሳም ዓለም አቀፍ፤ አህጉራዊ እና አካባቢያዊ የሠላም ማስከበር ተልዕኮዎችን ወስዶ ሕዝቡ ከጽንፈኛ እና ሽብርተኛ ቡድኖች የሚደርስበት ፈተና ለማቅለል፤ የተሻለ የሠላም አየር እንዲተነፍስ ለማስቻል ብዙ መስዋዕትነት የጠየቁ ወታደራዊ ተልዕኮዎችን ወስዶ በስኬት ተወጥቷል ።

በአሁናዊ ጉዳይ ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀስላሴ ፤ "ኢትዮጵያ በንጉሱ እና በደርግ የአስተዳደር ጊዜ በሶማሊያ የደረሰባትን ወረራ አትረሳም፣ ሕዝቦቿም ተላላ አይደሉም ብለዋል። አምባሳደሩ እንዳረጋገጡት ፣ የሶማሊያ ሰላም እኛን ይመለከታል፣ ሰላም እንዲመጣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት መስዋዕትነት ከፍሏል ። አሁንም የሶማሊያ ሁኔታ የሚያሳስበን ድንበር ዘሎ የሚመጣ ትርምስን ስለማንፈልግ ነው።

ይህም ሆኖ ግን ግብጽ በአዲሱ የውጭ ጉዳይ እና የመስኖ ሚኒስትሩ ዶ/ር ባዳረ አብዱላቲ በኩል ለተባበሩት መንግሥታት የጸጥታው ምክር ቤት በላከችው ደብዳቤ " ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝ ላይ እየገነባች ባለችው ግድብ ምክንያት የውሃ ደኅንነቴን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን እርምጃ የመውሰድ መብት አለኝ አለች " ስትል እንደተለመደው የጦርነት ዲቤ እያሰማች ትገኛለች።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት ባስመዘገበችው ታሪክ የውጭ ችግር ሲያጋጥማት ሕዝቦቿ በጋራ መመከት የተለመደ መሆኑ ይታወቃል። አሁንም በሞቃዲሾ የተዘረጉት የካይሮ የጥፋት እጆችን ለመመከት ካይሮ የአባይ ወንዝ ድብቅ አጀንዳ አንግባ በወታደራዊ ስምምነትና ከበባ፣ ኢትዮጵያን ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በማቃቃር፣ በዓለም አቀፍ ክስና እሩጫ የሚቀየር አቋም አይኖርም። እንዲያውም በቅርቡም የግድቡ ግንባታ "ሪቫን " መቆረጡ የሚጠበቅ ነው።

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የታላቁ የሕዳሴ ግድብ ሦስተኛውና አራተኛው ተርባይኖች ሥራ መጀመራቸው አብስረዋል። የዓባይ ወንዝ ፍሰቱ ሳይስተጓጎል መቀጠሉንና የግድቡ ማስተንፈሻ በሮች ተከፍተው በሰከንድ ተጨማሪ 2 ሺህ 800 ሜትር ኪዩብ ውኃ መፍሰስ መጀመሩ የፍፃሜውን መቃረብ ይጠቁማል።

በርግጥ በሀገሩ ሉአላዊነት ላይ የማይደራደረው ሕዝባችን ከመቼውም ጊዜ በላይ ጉዳዩን በንቃት እየተከታተለ ስለመሆኑ ብዙ ማለት አያስፈልግም። በብዙ ጩኸት መካከል ዓባይን መገደብና ሃይል ማመንጨት እንደቻልነው ሁሉ የባሕር በር ፍላጎታችንንም ብሔራዊ ጥቅማችንን ሳይጎዳ እንደምናሳካ እምነቴ ነው ። ለዚህ ደግሞ እስካሁን ያለን ሀገራዊ ዝግጁነት በቂ እና ከበቂ በላይ ነው።

> "
>
> **የሶማሊያ ባለስልጣናት አሁን ላይ የግብጽ ጦር በሶማሊያ እንዲሰማራ ከስምምነት መድረሳቸው "የናይል ጉዳይ" ወደ ሶማሊያ የሚያመጣ እና "በአፍሪካ ቀንድ ላይ አለመረጋጋት ሊያመጣ የሚችል" እንደሆነ የተረዱት አይመስልም። ቢያውቁትም ችግሩን አሻግረው ማየት ተስኗቸዋል። ችግሩ በአልሸባብ ፍዳውን ሲበላ የቆየውን የሶማሊያ ሕዝብን ዳግም ወደ ነበረበት መከራ የሚመልስ ነው**

# ስፖርት

## ከፓራሊምፒክ ጀግኖቹ አንደበት

ብርሃን ፈይሳ

ከቀናት በፊት የተጠናቀቀው የፓሪስ 2024 ፓራሊምፒክ በኢትደዮጵያ የፓሪሊምፒክ ዓለም አቀፍ ተሳትፎ ታሪክ በውጤታማነት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል። ኢትዮጵያን ፓሪስ ላይ የወከለው ቡድን በአራት አትሌቶች ተሳትፎ ሶስት ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብም በኦሊምፒክ ውጤት ለተከፋውን ሕዝብ ክሷል። በዚህም የፓራሊምፒክ ቡድኑ ወደ ከትናንት በስቲያ ሃገሩ ሲመለስ ደማቅ አቀባበል ተደርጎለታል።

ቡድኑ ከትናንት በስቲያ ንጋት ቦሌ ዓለም አቀፍ አየር መንገድ ሲደርስ በኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ሸዊት ሻንካ፣ የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወልደጊዮርጊስ ደማቅ አቀባበል አድርገውለታል። በ17ኛው የፓሪክ ፓራሊምፒክ ተሳታፊ የነበረው ቡድን ሁለት አሯሯጮችን ጨምሮ በስድስት አትሌቶች ተሳትፎ ሁለት የወርቅና አንድ የብር በጥቅሉ ሶስት ሜዳሊያ እንዲሁም ዲፕሎማ በማስመዝገብ መመለሱ ይታወሳል።

በ1ሺ500 ሜትር (ሙሉ በሙሉ ዓይነ ስውራን) የዓለም ክብረ ወሰንን 4፡27.68 በሆነ ሰዓት በመስበር አሸናፊ የሆነችው አትሌት ያየሽ ጌቴ፣ በተገኘው ውጤት ኩራትና ደስታ የተሰማት መሆኑን በአቀባበሉ ወቅት ተናግራለች። ውድድሩ ከባድ ቢሆንም ወደ ፓሪስ ከመሄዷ አስቀድሞም የወርቅ ሜዳሊያውን ለማሳካት እና ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ ማለሟ ውድድሩ ላይ የነበረውን ሁኔታ እንድትቋቋም አድርጓታል። በቀጣይም በዚሁ ስኬት ለመቀጠል እንዲሁም የምትሳተፍባቸውን ርቀቶች የመጨመር ፍላጎት ያላት ሲሆን፤ ለዚህም ጠንክራ



በፓሪስ 2024 ፓራሊምፒክ ውጤት ያስመዘገቡ ጀግኖች አትሌቶችና ልዑካን ቡድኑ አቀባበል ተደርጎለታል፣

እንደምትሰራ ገልፃለች። የፓራሊምፒክ ክለቦች እንደ ሃገር ቢቋቋሙ ደግሞ እሷን መሰል በርካታ ውጤታማ አትሌቶችን ለማፍራት እንደሚቻልም ጠቁማለች።

በኢትዮጵያ የፓራሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ በቶኪዮ ፓራሊምፒክ ላይ ያስመዘገበችው አትሌት ትዕግስት ገዛኸኝ ደግሞ፣ ፓሪስ ላይም ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ ማሳካቷ ይታወቃል። በ1ሺ500 ሜትር ጭላንጭል የተካፈለችው አትሌቷ በተከታታይ አሸናፊ ለመሆኗ በመድረኩ ያዳበረችው ልምድ የጠቀማት መሆኑን በማንሳት መደሰቷን ትናገራለች። ‹‹በተከታታይ የፓራሊምፒክ መድረኮች የወርቅ ሜዳሊያ መመዝገቡ እንዲሁም ቁጥሩ መጨመሩ በስፖርቱ መነቃቃትን የሚፈጥር ነው›› በማለትም በዚህ አቋም በተለያዩ ውድድሮች ተሳትፋ ሃገሯን ለማስጠራት ጠንክራ እንደምትሰራ ቃል ገብታለች።

በተመሳሳይ ርቀት በወንዶች ጭላንጭል ደግሞ አትሌት ይታያል ስለሺ የብር ሜዳሊያ ሊያስመዘግብ ችሏል። አትሌቱ በውድድሩ ውጤታማ ለመሆን በዝግጅት ላይ ሳለ ጉዳት ቢገጥመውም በዚህ ሳይረታ ሃገሩን ሊወክል ችሏል። እጅግ ፈታኝ በነበረው ውድድር አሸናፊ የሆነው ብራዚላዊ አትሌት ልምድ ያለው መሆኑ ክብረወሰን እስከማሻሻል ያደረሰው ሲሆን፤ በመድረኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳተፈው ይታያል ሁለተኛ ደረጃን እንዲይዝ አድርጎታል። ይህንን ልምድ ተመርኩዞም በቀጣይ ለሚኖሩት ውድድሮች ጠንካራና በሁለት ርቀቶች የሚሳተፍ አትሌት ለመሆን ጥረት ያደርጋል። ለአካል ጉዳተኛ ስፖርተኞች የሚደረገው ድጋፍ አሁንም አነስተኛ መሆኑን የሚጠቁመው አትሌቱ በፓሪስ የተካፈሉት አሌቶች አራት ብቻ ቢሆኑም የተገኘው ውጤት ስኬታማ ሊባል የሚችል ነው።

ነገር ግን እንደ ሌላው ሃገር በርካታ አትሌቶችን ማሰለፍ ቢቻል ተጨማሪ ውጤት ማግኘት ይቻላል። ሌሎች ዓለም አቀፍ የፓራሊምፒክ ውድድሮች ላይ ተሳታፊ በመሆን ልምድ ለማዳበርም አቅም የሚያስፈልግ በመሆኑ ስፖርቱ ትኩረት ያስፈልገዋል። እአአ በ2028 ለሚደረገው ፓራሊምፒክም ከአሁኑ መስራት እንደሚገባ የሚጠቁመው አትሌቱ፤ አቅመ ያላቸው ተቋማት ክለቦች ሊመሰረቱና አትሌቶችን ሊይዙ እንደሚገባም አስገንዝቧል። ይህ ከሆነም በአፍሪካ ደረጃ ቀዳሚ በዓለም ደግሞ ተፎካካሪ ለመሆን እንደሚቻልም አክሏል።

ለቡድኑ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት ሚኒስትሯ ሸዊት ሻንካ በበኩላቸው ‹‹ባመጣችሁት ውጤት ኮርተናል፣ በዓለም አደባባይ ሰንደቃችን እንዲውለበለብ፣ ገጽታችን እንዲገነባ እንዲሁም ስማችን በተደጋጋሚ እንዲጠራ ስላደረጋችሁ እናመሰግናለን። በዓለም አቀፍ ከዚህ ቀደም ከነበረው የፓራሊምፒክ ደረጃ የተሻለ ውጤት የተመዘገበ በመሆኑ እንደ መንግስት አካል ጉዳተኞችን በስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ የፖሊሲ አቅጣጫ አስቀምጦ በርካታ ስራ እየተከናወነ ይገኛል። ቡድኑ ሲጓዝም ድጋፍ ተደርጓል ወደፊትም በአትሌቲክስ ብቻም ሳይሆን በሌሎች ስፖርቶችም ተወዳዳሪ ስፖርተኞችን ለማፍራት በልዩ ሁኔታ ድጋፍ የምናደርግ ይሆናል። በቀጣይም በድል ለተመለሰው ቡድንን የሚመጥን ዕውቅና እና ሽልማት እናዘጋጃለን›› ብለዋል።